# ወልቃይትና አካባቢዉ፡- ጥያቄዉ የማን ነዉ? አፈታቱስ?

ብርሃነ በርሀ

መስከረም 7 ቀን 2009 ዓ.ም.

## 1. እንደመነሻ

የዓለም አቀፍ መሰረታዊ የሰብአዊ ሙብት ሀግጋትና መግለጫዎች የፈረሚም አልፈረሚም፤የአፅዳም አላፅዳቂም አገሮችና መንግስታት ጉዳይ ናቸዉ ይባላል። የሰዉ ልጆችን ህይወት የመጠበቅና ከአደጋ የመከላከል ጉዳይ ዜጋ በመሆንና ባለመሆን ልዩነት ሊደረግበት አይገባም ሲባልም ይደመጣል። በተለይ የሁለተኛዉ መሰረተሃሳብ መሰረታዊ ምክንያት አንድና አንድ ነዉ። በዚህች ዓለም ላይ ያሉ መንግስታትና አገሮች ከአገራቸዉ ርቀዉ የማይኖሩ ህዝቦችና ዜጎች የሉዋቸዉም።ሁሉም አገሮችና መንግስታት በህጋዊም ሆነ በህገወጥ መንገድ ከአገሩ ዉጭ የሚኖር ዜጋም ሆነ ተወላጅ አለዉ። በመሆኑም በዉስጣቸዉ የሚኖሩትን የሌላ አገር ዜጎችና ህዝቦች ህልዉና እና ደህንነት ከራሳቸዉ ዜጎች ባልተናነሰ ሁኔታ ጥበቃ ካላደረጉላቸዉ በሌሎች አገሮች የሚኖሩ ዜጎቻቸዉንና ተወላጆቻቸዉን ለአደጋ እንደማጋለጥ ይቆጠራል። በመሆኑም የሰዉ ልጆች ህልዉና በወንጀል ድርጊትና በአመፅ ሳቢያ እንዳይጠፋ የመከላከል ጉዳይ በዓለምአቀፍ ደረጃ የወጡት የሰብአዊ ሙብት ህግጋት በአገሮቹ ተቀባይነት አግኝተዉ ቢፀድቁም ባይፀድቁም ሌላዉ ቢቀር በልማዳዊ የህግ አስገዳጅነት አስተሳሰብ (customary International law) በሁሉም መንግስታት ላይ ግዴታን የመጣል ባህሪ አላቸዉ ተብሎ ይታመናል። ሁሉም ነዋሪዎች ያለምንም ስጋት እንዲኖሩ በአካባቢ፤በክልልና በአገሮች አስተዳዳሪዎች እና መንግስታት ላይ የመጠበቅ እና የመከላከል ግዴታ ተጥሏል። ከዚህ ርእስ ጋር ቀጥታ ተያያዥነት ባይኖረዉም አንድ ትዝብት ላቋድሳችሁ። በቅርቡ ነዉ። እጅግ ወደማከብረዉ እና ወዳሳደገኝ ህዝብ ጎራ ብዬ ነበር። ስለአካባቢዉ ሁኔታ ሀሳብ መለዋወጥ ጀመርኩ። ያገኘሁት መረጃ ግን በተጨባጭ ከሚታየዉና ከጠበቅሁት ዉጭ ነዉ። ምላሽ የሰጠኝ ሁሉ በስጋት የተዋጠ ነዉ። “ጦር ከፈታዉ ወሬ የፈታዉ” እንዲሉ የነዋሪዉ ዉስጣዊ ሰላምና ደህንነት ምንጩ በማይታወቅ ወሬ እና የፌዴራልም ሆነ የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት በማያዉቁት “የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ” ተሸብሯል። ስለፍርሃታቸዉ እና ስጋታቸዉ ጭብጥ ብጠይቃቸዉም ተጨባጭ መረጃ ማቅረብ አልቻሉም። ምን ሆናችሁ? ተብለዉ ሲጠየቁ “...የንግድ ድርጅታችሁን፤ ሱቃችሁን ....ለስድስት ቀናት እንዳትከፍቱ ተብለናል፤ ቅንጅት በምርጫ 97 ወቅት እንዳደረገዉ ለስድስት ቀናት ከቤት እንዳትወጡ ተብለናል.....ወዘተ።” ይህን ያዘዘዉ ማን ነዉ? ስራ እንዳትሰሩ ስለታገደበት እና ከቤት እንዳትወጡ ስለተከለከለበት ምክንያት ለምን አስተዳደሩን አትጠይቁም.....?”። “አስተዳደሩ እራሱ በስራ ላይ አይደለም፤ አስተዳደሩ እራሱ ፍርሃት ላይ ነዉ፤ በርካታ የገጠር ቀበሌዎችና ከፊል ከተማ አካባቢዎች እየተመሩ ያሉት በአገር ሽማግሌዎች ነዉ። በኦሮሚያ ክልል መንግስት የለም።እየተመራን ያለነዉ እነ ጃዋር በፌስ ቡክ በሚያሰራጩት ትእዛዝ እና መልእክት ነዉ....ወዘተ።” የሚገርመዉ እንዲህ አይነት መልስ ያገኘሁት ከተማረዉ የህብረተሰብ ክፍል ጭምር መሆኑ ነዉ። “ጦር ከፈታዉ ወሬ የፈታዉ ማለት” ይህ ነዉ። በበኩሌ ደርሼ እስክመለስ ያሳደገኝ ህዝብም ሆነ አካባቢ ከቀድሞዉ አልተለየብኝም።

በተንቀሳቀስኩባቸዉ ቦታዎች ሁሉ ህዝቡ እንደቀድሞዉ ሰላማዊ ነበር። ለምን ከቤት ወጣህ ያለኝ የለም። የበኩሌ ግምገማ ግን ይህን

*"ጦር ከፈታዉ ወሬ የፈታዉ"*

መልስ ከሰጡኝ ነዋሪዎች የተለየ ነዉ። በሰላማዊ ምርጫ ስልጣን መያዝ ያልቻሉ አካላት መሪዉን ድርጅት አህዴድንም ሆነ የክልሉን መንግስት በዉዥንብር እና በነዉጥ ለማተራመስ ከሚጠቀሙባቸዉ ስልቶች አንዱ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ። በተለይ የብሄር ብሄረሰቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት የማይቀበሉ ተቃዋሚ ሀይሎች ታሪካዊ መሰረቱ በሌሎች ክልሎች የሆነዉን የህብረተሰብ ክፍል ስጋት ዉስጥ እየከተቱት ነዉ። "ግርግር ለሌባ ይመቻል" እንዲሉ "...በተረጋጋ ስነልቦና እንዳትኖር ምክንያት የሆነህ የኢህአዴግ ስርአትና አስተዳደራዊ ርእዮተዓለም ነዉ " በሚል መልእክት የሽብር ዘመቻ መክፈታቸዉን መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም ህዝቡን ቀረብ ብሎ ማዳመጥ፤ማወያየትና እዉነታዉን ማስረዳት፤ ችግሮች ካሉም አፋጣኝ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በመቀየስ ከስጋት እንዲወጣ ማድረግ ለነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም። አለበለዚያ መድረኩ በህገመንግስታችን እና በስርአታችን ቀበኞች ቁጥጥር መዘዉር ስር ሊወድቅ ይችላል። ይህን መሰረተሃሳብ አስመልክቶ መደምደሚያዉ ላይ እስክንገናኝ ድረስ ወልቃይትን እና አካባቢዉን ወደተመለከተዉ የፅሑፉ መሰረታዊ ጭብጥ እናምራ።

# 2. ቅድመ ኢህአዴግ -በቁንፅል

በተለይ የህወሓት በአጠቃላይ ደግሞ የኢህአዴግ ትግል የመድሎ ስርአቶችን መገርሰስ ብቻ ሳይሆን የተዛቡ ታሪኮችንና የአስተዳደር መዋቅሮችንም በማረም ላይ ያተኮረ ነበር። ከደርግ እስከ ንጉሰነገስት አፄ ሚኒሊክ ድረስ የነበረዉን የአስተዳደር ስርአትና ታሪካዊ ዳራ ስንፈትሽ ደግሞ የአስተዳደር ስርአቶቹ የዚህች አገር ብሄር ብሄረሰቦች ማንነትና ህልዉና በገዥ መደቦች የጭቆና ማጥ ዉስጥ ተዘፍቀዉ እንዲጠፉ የሚተጉ ነበሩ። ይህ ፅሁፍ በዋናነት ወደሚያነጣጥረዉ ወደ ወልቃይትና አካባቢዉ ጉዳይ እናምራ።

መምህር ገብረኪዳን ደስታ "የትግራይ ህዝብና የትምክህተኞች ሴራ ከትናንት እስከዛሬ" በሚል ርእስ በ1998 ዓ.ም ባሳተሙት መፅሃፋቸዉ (ከገፅ 146-147) አፄ ሚኒሊክ የትግራይን ህዝብ አንድነትንና ህልዉናን ለማዳከምና ለማጥፋት ከወሰዷቸዉ እርምጃዎች አንዱ ህዝቡን ከነባር አስተዳደራዊ ይዞቶች ወደማይገባዉና ይሁንታዉ ወዳልተረጋገጠበት መልከኣምድራዊ አካባቢዎች ማካተት ነበር። እ.ኤ. አ. በ1894ና ከዚያ ቀደም በራስ ሓጎስ ይተዳደርና ጸለምት በሚል ስያሜ ይታወቅ የነበረዉን የወልቃይት ጠገዴ አካባቢ ከትግራይ አስተዳደር በመቁረስ የንግስት ጣይቱ ልዩ ግዛት እንዲሆን ስለማድረጋቸዉ ታሪክን አጣቅሰዉ ነግረዉናል። በወቅቱ በአፄ ሚኒሊክ የተወሰደዉ በአንድ ብሄር ጥላቻ ላይ የተመሰረተዉ የማዳከም(ህልዉናን የማትፋት) እርምጃ አስተዳደራዊ አካባቢን ከአንዱ ወደሌላዉ በማዛወር ላይ ብቻ የተመሰረተ አልነበረም። ከዚህ ይልቅ ህዝቡ ሀይማኖታዊም ሆነ አስተዳደራዊ ተግባራቱን የስር መሰረቱ በሆነዉ የትግርኛ ቋንቋ እንዳይጠቀምና በጊዜ ሂደት ማንነቱ፣ታሪካዊ ዳራዉ እና ባህሉ ተዳክሞ በሌሎች የበላይነት ደብዛዉ እንዲጠፋ ያለመ ነበር። ይህ የገዥዎችና የትምክህተኞች ሴራ ደግሞ

የአዉሮፓ ቅኝ ገዥዎች አስተዳደራዊ አካባቢዎችን ቆርሰዉና ቆራርሰዉ በፈጠሯቸዉ መልከአምድራዊ አሰፋፈሮች የአፍሪካዊያን ብሄሮችንና ብሄረሰቦችን ነባር ህልዉና የማጥፋት ተልእኮ ሌላኛዉ ገፅታ ነበር።

## *ህዝቡን ለመቅጣት ሲባል የወልቃይት ጠገዴ አካባቢን ከትግራይ አስተዳደር በመቁረስ የንግስት ጣይቱ ልዩ ግዛት እንዲሆን ተደርጎ ነበር*

አምባገነኑ እና አሳዉን ለማጥፋት ባህሩን ማድረቅ የሚል መርህ አንግቦ የትግራይን ህዝብ ደብዛ ለማጥፋት ሁለንተናዊ እርምጃዎችን ሲወስድ የኖረዉ የድርግ መንግስት በበኩሉ በተለይ በ1981/82 ተመሳሳይ እርምጃ ወስዷል። በህወሓት እና በሻዕቢያ ይደርስበት ከነበረዉ ሽንፈት የሚታደገዉ መስሎት አንዳንድ አካባቢዎችን በራስ ገዝ ስም የከፋፈለበት ወቅት ነበር። በዚህ ወቅት ሁሉንም ብሄር ብሄረሰቦች በአስተዳደራዊ መዋቅር ሳቢያ በመበታተን ስለመኖራቸዉ እንዳይታወቅና ተረስተዉ እንዲኖሩ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ወስዷል። ለምሳሌ ያህል ትግራይ፣ ጎጃም፣ ወሎ፣ ጎንደርና ሸዋ በተሰኙት ክፍለሀገራት ሳቢያ የብሄር ብሄረሰቦችን ህልዉና በየቦታዉ በመበታተን እንዲጠፋ ተደርጓል።የአፋርን ብሄረሰብ አንድም ከትግራይ አለያም ከሌላዉ አሰተዳደር አካባቢ ጋር በመበረዝ በዚህች አገር ዉስጥ ማንነቱ እና ህልዉናዉ ተረስቶ እንዲኖር ተበይኖበታል። የቤኒሻንጉል ብሄር ብሄረሰብ አንድም ከጎጃም አለያም ከሌላዉ ክፍለሀገር ጋር በመበረዝ ህልዉናዉ የሚያከትምበት አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዶበታል። በሀረር ክፍለሀገር የተጨፈለቁት ህዝቦችም ቢሆኑ በእንድ ቋንቋና አሀዳዊ አወቃቀር ስርአት ሳቢያ ዛሬ የብዙህነታችን ዉበት አካል የሆነዉ ማንነታቸዉ ጎልቶ እንዳይወጣ ተደርጓል። የሱማሌ ብሄረሰብ ስለመኖሩ የሚታወስበት አስተዳደራዊ ስልጣን አልተሰጠዉም ቋንቋዉንና ባህሉን የሚያሳድግበት ቅድመሁኔታ አልተመቻቸለትም። ዛሬ ወልቃይት እየተባለ የሚጠራዉ አካባቢ ነወሪ የነበረዉና በተለያዩ ማስረጃዎች ማንነቱ የትግራይ ህዝብ አካል እንደሆነ የሚረጋገጥለት ህዝብም ቢሆን በተመሳሳይ እርምጃ ያለይሁንታዉ በአስተዳደራዊ አወቃቀር ሳቢያ እንዲሰደድ ተፈርዶበት ነበር።

# 3. ድህረ ደርግ-በጨረፍታ

የህወሓት/ኢህአዴግ የትግል ዉጤትም እነዚህን ብሄር ብሄረሰቦች ደብዛ ለማጥፋት ጭምር ያለሙ የአስተዳደር ስርአቶችን ለማረም ያስቻለ ነዉ። አሰፋፈርንና የብዙሃን ፍላጎትን መሰረት በማድረግ ጎልተዉ እንዲወጡና ወደታሪካዊ ቦታቸዉ እንዲመለሱ አድርጓል። ይህ እርምጃም በሽግግር መንግስቱ በ1992 ከወጣዉ የራስን እድል በራስ የመወሰን ሙብት በሚያረጋግጠዉ አዋጅ ቁጥር 7 የተጀመረ ነዉ። በ1987 የአገሪቷን ብሄር ብሄረሰቦች በሚወክሉ ተሳታፊዎች መጠነ ሰፊ ዉይይቶች ተደርገዉበት የፀደቀዉ የኢፌዴሪ ህገመንግስትም ይህንኑ ይበልጥ በማጠናከር ስራ ላይ እንዲዉል አድርጓል። የኢህአዴግ መስራች ድርጅቶችም በህገመንግስቱ መሰረት የተዋቀሩት ክልሎች የተዛመደ አሰፋፈርን፣ተመሳሳይ ልምድን፣ባህልንና በአጠቃላይ ደግሞ የማንነት መገለጫዎችን መሰረት አድርገዉ የብዙሃን ሉአላዊነትን በሚያረጋገጥ አኳኋን የተዋቀሩ መሆናቸዉን አምነዉበት ሲተገበሩት ቆይተዋል። በሂደት ችግሮችና ጥያቄዎች ሲያጋጥሙ የሚፈቱበት ህገመንግስታዊና ተቋማዊ ስርአትም አስቀድሞ ተመቻችቷል፤ስራ ላይ ዉሏል። ባለፉት 25 ዓመታት ዉስጥም በየክልሉና በክልሎች መካከል የተከሰቱ ጥያቄዎች ህገመንግስታዊ ስርአቱንና አሰተዳደራዊ አወቃቀሮችን መሰረት አድርገዉ ሲፈቱ ቆይተዋል። ለመጥቀስ ያህል በሱማሌ እና ኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት 700 ቀበሌዎች በሚያካትቱ አካባቢዎች የመኖሪያ አካባቢን የመወሰን ጥያቄ (የድንበር ጥያቄ) ተነስቶባቸዋል። የክልሎቹ መንግስታት ባደረጉት ዉይይት ያለመግባባት ያስከተሉትን የድንበር አካባቢዎች ከ700 እንዲቀንሱ ካደረጉ በኋላ ከፌዴሬሽን ምክር ቤት ጋር

በመተባበር በቀሪዎቹ ላይ ህዝበ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ተደርጓል። “ስልጤ ስልጤ እንጂ ጉራጌ አይደለም” በሚል መሪ ቃል ማንነትን ለማስከበርሌተካሄደዉ የፖለቲካ ትግል ህገመንግስታችን እና ሌሎች ህግጋትን መሰረት በማድረግ በድል ተጠናቋል። በድል መጠናቀቅ ብቻ ሳይሆን የስልጤ ህዝብም ሆነ ህዝቡን ወክሎ ሲንቀሳቀስ የነበረዉ ፖለቲካ ድርጅት ክልሉን የሚመራዉ ፖለቲካ ድርጅትና ኢህአዴግ በእርግጥም ለብሄር ብሄረሰቦች ማንነትና ህልዉና በተግባር የቆሙ መሆናቸዉን ስላረጋገጠ የቀድሞ ህልዉናዉን በማጥፋት ዛሬ ደኢህዴን ብለን የምንጠራዉ ክልሉን የሚመራዉ ድርጅት ዉስጥ በራሱ ፍላጎት ተጠቃሏል። ከዚህ በተጨማሪም ክልሎች በዉስጣቸዉ ያሉና በልዩ ሁኔታ እራሳቸዉን በራሳቸዉ ሊያስተዳድሩ ለሚገባቸዉ ብሄረሰቦች ልዩ ዞን በመመስረት መብታቸዉን አረጋግጠዉላቸዋል። በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ኦሮሚያ እና የአዊ ዞን በምሳሌነት ሊጠቀስ ይችላል። የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ብሄረሰቦችን መሰረት ያደረጉ አስተዳደራዊ ዞኖችን ከማዋቀር በተጨማሪ የብሄረሰቦች ምክር ቤት በማቋቋም ብሄሮች ማንነት እና ሁለንተናዊ መብቶች የሚጠበቁባቸዉን ስርአቶች አመቻችቷል። እጅግ ፍትሃዊ ሆነዉ ሀረሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ህገመንግስትና ህዝብ የኦሮሞን ህዝብ መብት ለማስጠበቅ የሚያስችል ምክር ቤት አቋቁሟል። የቅርቡን ብንጠቅስ የቅማንት ብሄረሰብ ጉዳይ በህጋዊ መንገድ መፍትሄ ተሰጥቶበታል።እነዚህ ሁሉ እርምጃዎች ተግባራዊ የሆኑት ይህን ለማድረግ የሚያስችል ፖለቲካዊ ስርአት ከወዲሁ በመረጋገጡ ነዉ። ችግሮች ከመከሰታቸዉ በፊትም ሆነ ከተከሰቱ በኋላ በሰላማዊና በህጋዊ መንገድ መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችሉ ህጋዊም ሆነ ተቋማዊ ስርአቶች ተዘርግተዉ እየተሰራባቸዉ ነዉ። የወልቃይትና አካባቢዉ ጉዳይም በዚህ መነፅር የሚታይና መፍትሄ የሚሰጠዉ ነዉ።

# 4. የማንነት ወይንስ የድንበር ጥያቄ?

ወልቃይትንና አካባቢዉን አስመልክቶ የሚነሱ ጉዳዮች ሊኖሩ ቢችሉ አይደንቅም። በየትኛዉም ጊዜ በአንድ ግለሰብም ሆነ በህዝብ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ቢሆንም ግን እኛን የሚያሳስበን ጉዳይ፡-

- ጥያቄዉ የአገሪቷ ህግጋት እና መንግስት እና ተቋማዊ አሰራሮችን መሰረት አድርጎ የቀረበ ነዉ ወይንስ በህገወጥ መንገድና በህገወጥ ሀይሎች፤
- የህዝብን ሉኣላዊነትን መሰረት ያደረገ ነዉ ወይንስ የብዙሃን ሉኣላዊነትን በጥቂቶች ፍላጎት ለማፈን ያነጣጠረ የትምክህተኞች ጥያቄ ነዉ፤
- አንድን ክልል ወይንም መንግስት በሚያስተዳድር የፖለቲካ ድርጅት ዉስጥም ጭምር ተሰግስገዉ ህገመንግስታዊ ስርአትን በማፍረስ ወደቀድሞዉ ስርአታችን ለመመለስ በተቃኙ ግለሰቦችም ጭምር ግፊት የቀረበ ነዉ ወይንስ በስርአቱ እዉነተኛ ጠበቆች
- የማንነት ወይንስ የመኖሪያ አካባቢን የመወሰን ፍላጎት/የድንበር ጥያቄ/?

የሚሉት የልዩነት መሰረተሃሳቦች ናቸዉ።

## 4.1 የማንነት ጉዳይ

እስከአሁን ባለን መረጃ ጥያቄዉ የማንነት ይሁን የድንበር አለመግባባት በግልፅ ተለይቶ አልቀረበም። በአንድ በኩል በአገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ ያሉት “...ወልቃይት ጠገዴ ጎንደር እንጂ ትግራይ ሆኖ አያዉቅም....” በሚሉ መልእክቶች የታጀቡና የሀይል

እርምጃ እንዲወሰድ የሚጋብዙ ሰልፎች ተስተዉለዋል። በሌላ በኩል የወልቃይት ህዝብ አማራ እንጂ ትግራይ አይደለም የሚሉ የማንነት ጥያቄ የሚመስሉ ነዉጥ አዘል ማነሳሳቶች ተቀጣጥለዋል።

የማንነትን ጉዳይ እናስቀድም። በኢፌዴሪ ህገመንግስትም ሆነ በኢህአዴግ ስርአት የአንድ ግለሰብም ሆነ ብሄረሰብ የማንነት ጉዳይ ለድርድ አይቀርብም። አንድ ሰዉም ሆነ ቡድን በተለያየ ምክንያት ከበቀለበት ህብረተሰብ ርቆ ቢኖርም እንኳ ስለማንነቱ የሚወስነዉ ግለሰቡ ቡድኑ ወይንም ብሄር/ብሄረሰቡ ነዉ። እንደቀድሞዎቹ ስርአቶች ቋንቋህንና ባህልህን ለምን አራመድክ ተብሎ የማስፈራራትም ሆነ የእስራት ተግባራት አይፈፀምበትም። በሚኖርበት አስተዳደራዊ ክልል ዉስጥ ትግራይነቱን፣አማራነቱን፣ኦሮሞነቱን፣ ወላይታነቱን ወዘተ ጥያቄ ዉስጥ የሚያስገባ አይኖርም። የማንነት ህልዉናን የሚፈታተን ፖለቲካዊ እርምጃ አይወሰድበትም። አማራነትህን፣ተግራይነትህን፣ወላይታነትህን፣ሶማሌነትህን ወዘተ ለምን አወጅክ በሚል ጭቆና የሚያደርስ አስተዳደራዊ ስርአት የሰፈነበት ክልል ካለ ያ ክልል ህገመንግስታዊ ስርአታችንን በሚያከብርና በተቀበለ የፖለቲካ ድርጅት የሚተዳደር አይደለም። በቅደምተከተል የትግራይ እና የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ ህገመንግስታት አንቀፅ 91 እና 109 የብሄር፣ ብሄረሰቦችንና ህዝቦችን ማንነት ማክበር፣በመካከላቸዉ እኩልነትን እና አንድነት ማጠናከር የክልሎቹ መንግስታት ፖቲካ ነክ ዓላማዎች ስለመሆናቸዉ በግልፅ ይደነግጋሉ። ከዚህ በተጨማሪም የክልሎቹ መንግስታት _በዲሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመስረት_ ህዝቡ ራሱን በራሱ ማስተዳደር የሚያስችለዉን ስርአት ማስፈን እንዳለባቸዉ አፅንኦት ሰጥተዋል። ብሄር ብሄረሰቦች መራሳቸዉ መልከኣምድራዊ ክልል ዉስጥ የራሳቸዉን ጉዳይ በራሳቸዉ ለመወሰን የሚያስችላቸዉ አስተዳደራዊ መዋቅር ሲመሰረትም፡-

- *ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል*
- *ተመሳሳይ ልምዶች ያሏቸዉና ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸዉ*
- *የጋራ ወይም የተዛመደ ህልዉና ያላቸዉ*
- *የስነ ልቦና አንድነት ያላቸዉ እና*
- *በአብዛኛዉ በተያያዘ መልከአምድር የሚኖሩ*

ስለመሆናቸዉ ግምት ዉስጥ እንደሚገባ የሁለቱም ብሄራዊ ክልሎች ህገመንግስታት ተደንግገዋል።

በዚህ መሰረተ ሃሳብ ምክንያትም የራሱን እድል በራሱ እንዲወስን በህገምንግስትም ሆነ በብዙሃን ሉኣላዊነት አስተሳሰብ እራሱን የራሱን እድል በራሱ እንዲወስን ስልጣን የተሰጠዉ ህዝብ በመረጠዉ ቋንቋ የመተዳደር መብቱ የተጠበቀ ነዉ። ስለሆነም በዚህ ምክንያት ታሪካዊ ምንጫቸዉ ሌላ አካባቢ የሆኑ ግለሰቦችም ሆኑ አናሳ ብሄር ብሄረሰቦች የክልሉ ብዙሃን ህዝብ በወሰነዉ ቋንቋ እንዲተዳደሩና እንዲሰሩ በመደረጋቸዉ ምክንያት ማንነታቸዉ ተጥሷል ሊባል አይችልም። ምክንያቱም የአከላለል ስርአታችንም ሆነ የዲሞክራሲ ፅንሰሃሳብ ቅድሚያ የሚሰጠዉ አሰፋፈርን እና የነባር ህዝቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ነዉ። ይህ መብት በተረጋገጠበት ሁኔታ የልዩ ልዩ አናሳ(በቁጥር) ብሄር ብሄረሰቦች ማንነትም እንዲከበር አቅም በፈቀደ መጠን ጥረቶች ይደረጋሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ ልዩ ልዩ ብሄር ብሄረሰቦችን የሚወክሉ ከነባር ብሄር ብሄረሰብ ጋር በመጤነት የሚኖሩ

አናሳዎች(በቁጥር)  እራሳቸዉን ከአስተዳደር ስርአቱና ከነባሩ ብሄርና ብሄረሰብ ባህልና ቋንቋ ጋር የማዋሃድ የዉዴታ ግዴታ ተጥሎባቸዋል።

በአሁኑ ወቅት በትግራይ ክልላዊ መስተዳድር ስር ወልቃይት፣ፀገዴ፣ ቃፍታ ሁመራ እና ፀለምት የተሰኙ የአካባቢ መጠሪያዎችን በሚያካትተዉ ወረዳ ዉስጥ የሚኖሩ ህዝቦችን ማንነት ስንመለከት ደግሞ፡-

## 4.1.1 የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ሪፖርቶች

ሀ. በ1987 የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ዉጤት መሰረት ከ296,352 የወረዳዉ ህዝብ ዉስጥ 261,642(88%) ትግራይነታቸዉን አረጋግጠዋል። ከቀሪዉ ህዝብ ዉስጥ 31,142(10%) አማራነቱን አረጋግጧል። ይህ መረጃ ከቃፍታ ሁመራ፣ከፀለምት፣ ከወልቃይት እና ከፀገዴ ህዝብ ዉስጥ የተገኘ ድምር ዉጤት ነዉ።

ለ. የወልቃይትን እና የፀገዴን ህዝብ ብዛት ለብቻ ስንመለከት ደግሞ በድምር 150,032(ሲስተካከል-149,594) ስለመሆኑ የ1987 የቆጠራ ዉጤት ያመለክታል። ከዚህም ዉስጥ 132,631(በአማካይ 88.7%) ትግራይነቱን እና 16,960(11%) አማራነቱን ስለማረጋገጡ ሪፖርቱ ያስረዳል።

ሐ. በ1987 መረጃ መሰረት የወልቃይት ህዝብ ብዛት 90186 ነበር። ከዚህ ዉስጥ 87099(በአማካይ 97%) ትግራይነቱን፤ 2734(በአማካይ3%) አማራነቱን አረጋግጧል። በ1999/2000 በተካሄደዉ ቆጠራ መሰረት የወልቃይት ነዋሪ 138926 ነበር። በ1987 ቆጠራ መሰረት የተመዘገቡትን የትግራይ እና አማራ ነዋሪዎች የመቶኛ ድርሻ መሰረት አድርገን ብናሰላዉ በ1999/2000 ከተቆጠረዉ 138 926 የወልቃይት ነዋሪ ዉስጥ በአማካይ 96.7% ትግራይ 3% አማራ መሆኑን መገመት ይቻላል።

መ. በ1987 በተካሄደዉ ቆጠራ ከ59 846 የፀገዴ ህዝብ ዉስጥ 45532(በአማካይ 76%) ትግራይነቱን እንደዚሁም 14 226( በአማካይ 24%) አማራነቱን አረጋግጧል። በ1999/2000 በተካሄደዉ ቆጠራ  የፀገዴ ህዝብ ብዛት 103852 ነበር።

### *በአማካይ 97% የሚሆነዉ የወልቃይት ወረዳ ነዋሪ ትግራይነቱን አረጋግጧል*

እነዚህ መረጃዎች የሚያሳዩን በወረዳዉ የሚኖረዉ ህዝብ ማንነቱን በራሱ ጊዜ የወሰነ መሆኑን ነዉ ። በቁጥር ጭምር ተጠቅሶ የትግራይነቱ፣አማራነቱ ወይም ሌላ ብሄረሰብ ተወላጅነቱ ተረጋግጦለታል። የኢፌዴሪም ሆነ የክልሉ ህገመንግስትና አስተዳደራዊ ስርአትን እስካከበረ ድረስ ማንነቱን አስጠብቆ የመኖር መብቱ ተረጋግጧል። የክልሉ ህገመንግስትና አስተዳደራዊ ስርአት በሚፈቅደዉ መሰረት የመስራትና ሀብት የማፍራት መብቱም እንደዚሁ።በቋንቋዉ እናዳይናገር፣ባህልና ወጉን እንዳያራምድ ማእቀብ አልተጣለበትም። በዚህ ረገድ በማስረጃ የተደገፈ የመብት ጥሰት ስለመኖሩ እና  ለሚመለከተዉ አስተዳደራዊ አካል ስለመቅረቡ የሚያስረዳ ማስረጃ አልተገኘም። በ1987ም ሆነ በ1999/2000 ቆጠራ ዉጤት መሰረት በአማካይ  97% የሚሆነዉ የወልቃይት ነዋሪ ትግራይነቱን ያረጋገጠ ከሆነ ይህ

ህዝብ ከዚያ በኋላ ተፀፅቶ የሌላ ብሄር ማንነት እንዲሰጠዉ ጥያቄ ያቀርባል ተብሎ አይታመንም። የማንነት ጥያቄዉን እያነሱ ያሉት በወቅቱ ቆጠራ መሰረት 3% የሚሆኑት አማራነታቸዉን ያረጋገጡት ነዋሪዎች ናቸዉ የሚባል ከሆነ ደግሞ በአንድ በኩል ማንነታቸዉን አስቀድመዉ ያረጋገጡ መሆናቸዉ ሪፖርቱ ያስረዳል። በሌላ በኩል ደግሞ የማንነት ጉዳይ እራስን በራስ ከማስተዳደር መብት እና የመኖሪያ አካባቢን ከመወሰን ጋር በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ስለሚተሳሰር 3% የሚሆነዉ አማራነቱን ያረጋገጠ ህዝብ የ97%ን የብዙሃን ሉኣላዊነት በመጨፍለቅ ወደአጎራባች ክልል እንዲዋሰን ወይንም ደግሞ በትግራይ ክልል ዉስጥ (ለምሳሌ ልክ እንደስልጤ ብሄረሰብ) እራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር ልዩ ወረዳ/ዞን ወይንም አስተዳደር ክልል ሊዋቀርለት ይገባል የሚል አቋም ሊራመድ አይችልም። ይህ ሊሆን የማይችልበት ምክንያት በመጀመሪያ ደረጃ 3% የሚሆነዉ አማራ የሚኖርበት ወልቃይት ታሪካዊ ዳራዉ እና የአሰፋፈር መለኪያዉ ወደትግራይ እንጂ ወደአማራ ሊካለል የሚገባዉ አይደለም። በሁለተኛ ደረጃ ይህ ህዝብ ህገመንግስታችን ማንኛዉም ሰዉ ከቦታ ወደቦታ ተዘዋዉሮ መስራት እና ሀብት ማፍራት እንደሚችል በደነገገዉ መሰረት በትግራይ ክልል ዉስጥ ይህ መብቱ ተጠብቆለት ሊኖር የሚገባዉ ነዉ። በመሆኑም በክልሉ ዉስጥም ቢሆን የራሱን የአስተዳደር ክልል እስከመመስረት ድረስ የሚያደርስ ማንነቴ ይረጋገጥልኝ የሚያሰኝ ጥያቄ ቢቀርብ ህገመንግስታችንም ሆነ የራስን እድል በራስ የመወሰን መርሃችን አይፈቅድም።

## *በአማካይ 3% የሚሆነዉ የወልቃይት ነዋሪ አማራነቱን አረጋግጧል*

ከላይ እንደተጠቀሰዉ ክልላዊ መንግስታት የብሄር ብሄረሰቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን እና የማስተዳደር መብት ማስጠበቅ አለባቸዉ። ራስን በራስ ለማስተዳደርም ሆነ ለአስተዳደራዊ አመቺነት በመስፈርትነት የሚያገለግለዉ የማንነት ጉዳይ ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህልን፣ተመሳሳይ ልምዶችን፣ የጋራ ቋንቋን፣የጋራ ወይም የተዛመደ ህልዉና፣የስነ ልቦና አንድነትን እና የተያያዘ መልከአምድርን ግምት ዉስጥ የሚያስገባ ነዉ። ከ97% በላይ የሚሆነዉ ትግራይነቱን ያረጋገጠዉ የወልቃይት ነዋሪ ህዝብ በእነዚህ መስፈርቶች ሲመዘን ሊካልልም ሊዛመድም የሚችለዉ ወደቀሪዉ የትግራይ ህዝብ እንጂ በቋንቋም ሆነ በሌሎች ባህላዊ እና ዲሞግራፊያዊ መለኪያዎች ከማይዛመደዉ(ከትግራዩ ጋር ሲነፃፀር) በአማራ ብሄራዊ ክልል ዉስጥ ከሚኖረዉ ህዝብ ጋር አይደለም። ስለሆነም ዉስጥ የሚኖረዉ ከ3% የማይበልጠዉ አማራነቱን ያረጋገጠዉ ህዝብ የ97% የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት የሚያፍን ሉኣላዊ ስልጣን ሊሰጠዉ አይችልም። ለ3% ሲባል የ97% ብሄረሰብ ማንነትና አስተዳደራዊ መብት የሚረገጥ ከሆነ "መንግስት *<u>በዲሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመስረት</u>* ህዝቡ ራሱን በራሱ.." እንዲያስተዳድር ሁኔታዎችን ሊያመቻቹ እንደሚገባ በሁለቱም ክልሎች ህገመንግስታት ላይ የሰፈረዉ ፖለቲካዊ ነክ ዓላም ይጣሳል። ስለዚህ በወልቃይት ዉስጥ የሚኖሩት ትግራይነታቸዉን ያላረጋገጡት ብሄረሰቦች ምርጫ አንድም እኩልነታቸዉ፣ ማንነታቸዉና ሌሎች መብቶቻቸዉ ተጠብቆ ነገር ግን የራሱን እድል በራሱ እንዲወስን ስልጣን የተሰጠዉን ብሄር ብሄረሰብ ለማስተዳደር የወጡትን አስተዳደራዊ እና ህገመንግስታዊ መርሆዎች አክብረዉ መኖር ነዉ። ካልሆነም ደግሞ(በዚህ ሁኔታ መኖር አመቺ ሆኖ ካላገኙት) በፌዴራልም ሆነ በክልሎቹ ህገመንግስታት በሰፈረዉ የዘዋወር መብት መሰረት የመኖሪያ አካባቢያቸዉን የመቀየር መብታቸዉ የተጠበቀ ነዉ። *ይሁን እንጂ የህዝቦች በአንድነትና በእኩልነት መንፈስ አብሮ የመኖር ጉዳይ በህግ ክርክር እንዲወሰን ማድረግ ተመራጭ አይደለም።በህግና ህግጋቱን በሚያስፈፅሙ የግልግል ተቋማት አማካኝነት የሚሰጥ ዉሳኔ በተወሰነ ደራጅም ቢሆን የአሸናፊነት እና ተሸናፊነት ስሜትን ማሳደሩ አይቀርም። ይህ ደግሞ በህዝቦች መካከል መጠነኛ ቁርሾን የመፍጠር እድል አለዉ። ከዚህ ይልቅ*

*አቤቱታ አቅራቢዎች በአስተዳደር ስርአታችን እና ህገመንግስቶቻችን ተቀባይነት የሌላቸዉን የማንነትም ሆና የራስን እድል በራስ የመወሰን ጉዳዮች በቅን ልቦና ተመልከተዉ ቢተዉዋቸዉ ተመራጭ ይሆናሉ። በዚህ ሊፈታ የማይችል አሳማኝ ጭብጥ ካለ ደግሞ የክልል መስተዳድሮች በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠዉ መፍታት ይጠበቅባቸዋል። በዚህ መንገድ ከተጓዝን በዚህች አገር ዉስጥ ከልዩነቶቻችን ይልቅ በአንድነታችን እና በእኩልነታችን ላይ እንድናተኩር ይረዳናል። በዚህች አገር አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መገንባት የምንችለዉ የህገመንግስቶቻችንን የመሰረት ድንጋዮች በማክበር ለአብሮነታችን ልንጠቀምባቸዉ ከቻልንና በዚሁ መንገድ መትጋት የቻልን እንደሆነ ነዉ። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በለኮሱት እሳት ለአማራ ህዝብ ሀብትና ንበረት መዉደምም ሆነ ለንፁኃን ዜጎች ህልፈት ምክንያት ሆኑ ስርአት አልበኞች እና ወነጀለኞች ተጠያቂ መሆን ይኖርባቸዋል።*

ጭብጣዊዉ አመክንዮ ይህ ከሆነ በዉጭም ሆነ በክልሎች ዉስጥ የሚኖሩ ቡድኖች የ“አንድ ህዝብ፣ አንድ ቋንቋ፣ አንድ ሀይማኖት” ተምሳሌት የሆነዉን የቀድሞዉን ሰንደቅዓላማ እያዉለበለቡ ወልቃይትን የሚመለከት የማንነትም ሆነ እራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ ቢያነሱና ለየትኛዉም አካል ቢቀርብ ምላሹ ከወዲሁ የታወቀ ነዉ። እስከአሁንም በዚህ ረገድ የተፈፀመ የብሄር ጭቆና አለመኖሩን ከፍ ብሎ ከቀረበዉ አመክንዮ እና መረጃ መገንዘብ ይቻላል ። እንደቀድሞዎቹ ስርአቶች በግድ ትግራዋይ ሁን ወይም ወላይታ ሁን ወይም ኦሮሞ ሁን ወዘተ የሚል የጭቆና አስተዳደር እስከሌለ ድረስ ማንነት ተነካ የሚል ፉከራና ቀረርቶ ቢደመጥ ምክንያታዊ አይሆንም። የራስን እድል በራስ ለስከማስተዳደር የሚያበቁ የዲሞግራፊ ጭብጦች ችስከሌሉ ድረስ የማንነት ጉዳይ ለዚህኛዉም መብት በመነሻነት ሊያገለግል አይችልም። ስለሆነም የጥያቄዉ እና የሁከቱ ምንጭ ዛሬም ድረስ ታጥበን ያልጸዳነዉ ትምክህትና የጭቆና አባዜ ከመሆን አያልፍም። በትግራይ ክልል ዉስጥ በመካሄድ ትምክህት በወለደዉ ሰላማዊ ሰልፍ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ዉስጥ የሚኖር ከ90 % የሚልቅ

## *ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በለኮሱት እሳት ለአማራ ህዝብ ሀብትና ንበረት መዉደምም ሆነ ለንፁኃን ዜጎች ህልፈት ምክንያት ሆኑ ስርአት አልበኞች እና ወነጀለኞች ተጠያቂ መሆን ይኖርባቸዋል*

መሰረታዊ ምንጩ በክልሉ ዉስጥ የሆነዉን የአማራ ህዝብ መብት የሚጥስ ምላሽ ማግኘት አይቻልም። ከ90 % አማራ ጋር በሚኖሩ ጥቂት ትግራዮች ምክንያት የ90% አማራ ማንነት ትግራይ ይሁን ወይም የክልሉ የስራ ቋንቋ ትግርኛ ይሁን ወይም ደግሞ የጥቂቶቹ ትግራዮች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ይረጋገጥ የሚል ጥያቄ ሊቀርብ አይችልም። ይህ ሊሆን እንደማይችለዉ ሁሉ ከትግራይ አስተዳደር ዉጭ ያለ የነዉጥ አካል የትግራይ ክልል አካል የሆነዉን ከ97% ወይም ከዚህ የሚልቀዉን የወልቃይት ነዋሪ ማንነት ወይም የራስን እድል በራስ የመወሰን አጀንዳ ይዞ ሊከራከርም ሆነ ሊወስን አይችልም። እንዲህ አይነት ትምክህት የወለደዉ የነዉጥ ሰልፍ በአዲስቷ ኢትዮጵያ ተቀባይነት አይኖረዉም።

## 4.1.2 የደርግ ወቅት መረጃ

በደርግ ጊዜ የወልቃይትና ጠገዴ ወረዳዎች ነዋሪ ትግራዋይ እንደነበር ደርግ እራሱ ነግሮናል። ከደርግ በላይ ምስክር ማንንም ልንጠራ አንችልም። በአሁኑ ወቅት በተለይ በጎንደር አካባቢ የወልቃይትንና ጠገዴን አስታኮየተነሳዉ ሁከት የእነ መላኩ ተፈራ አልሞት ባይ አስተሳሰብ ድብልቅ ዉጤት ነዉ። በተለይ በብሄረሰብ ላይ ያነጣጠረዉ የጥፋት ዘመቻ እና ደም የማቃባት ተግባር የክልላዊም ሆነ አገር አቀፋዊ መንግስት ስርአትን ለማፍረስ ያለሙ እኩዮች ሴራ በመሆኑ ተልእኮዉ በራሳቸዉ ማስረጃ እና ዱላ መመታት ይኖርበታል። በወቅቱ ያረጋገጡት መምቻ ዱላቸዉም የሚከተለዉ ነዉ።

እና በትግራይ እና አማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት ህገመንግስቶች መሰረት ወደትግራይ ክልል ተዋሰነ። የቀድሞዉ የትግራይ ክልል ፕሬዚደንት አቶ ገብሩ አስራት ሳይቀሩ ከሪፖርተር ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ፡-

## *የመሬትና የሀብት ዝርፊያ ቢሆን ኖሮ ከሁመራ አካባቢ ይልቅ የጨው ....፣ የፖታሽ ....እና ሌሎች ውድ ማዕድናት ያሉበት ከትግራይ ወደ አፋር የተካለሉት አምስት ወረዳዎች ይበልጣል*

**" ...ወልቃይት .....በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት መሠረት ......ቋንቋን፣ ባህልን፣ አሰፋፈርን....መሠረት አድርጎ የተካለለ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የወልቃይት ሕዝብ ትግርኛ ይናገራል፡፡ የፀገዴም ሕዝብ ግማሹ ትግርኛ ይናገራል፡፡ ትግርኛ ተናጋሪው ፀገዴ ወደ ትግራይ ተካሏል፡፡ አማርኛ ተናጋሪው (ጠገዴ) ደግሞ ወደ አማራ ክልል ተካሏል፡፡ ከትግራይም አገውኛ የሚናገር ወደ አማራ ክልል ተካሏል፡፡ የአፋር ክልል ከወሎና ከትግራይ ተዉጣጥቶ የተካለለ ነዉ። በቀድሞዉ የትግራይ ራስ ገዝ ስር የነበሩ አፋርኛ ተናጋሪ ህዝብ ነበረባቸዉ አምስት ወረዳዎችም ወደ አፋር ክልል ተቀላቅለዋል፡፡ የአከላለሉ መነሻ ምክንያት የሀብት ወይም የመሬት ዝርፊያ አለመሆኑን ማረጋገጥ እፈልጋለሁ፡፡ የመሬትና የሀብት ዝርፊያ ቢሆን ኖሮ ከሁመራ አካባቢ ይልቅ የጨው ....፣ የፖታሽ ....እና ሌሎች ውድ ማዕድናት ያሉበት ከትግራይ ወደ አፋር የተካለሉት አምስት ወረዳዎች ይበልጣል፡፡ ቀዳሚዉ መስፈትር ሀብት ሳይሆን የራስን እድል በራስ የመወሰን እና የብሄሮችን ማንነት የሚያጎለብቱ አስተዳደራዊ ክልሎችን መፍጠር በመሆኑ አፋርኛ ተናጋሪ ዉ ህብረተሰብ ....ወደ አፋር ተካለለ። ወልቃይት ደግሞ ትግርኛ ተናጋሪ በመሆኑ ወደ ትግራይ ተካለለ፡፡ .....በዚህ የአከላለል ሥልት ድሮ የነበረው ተለውጧል፡፡ ይህ አከላለል በትግራይ ብቻ[ የተፈፀመ ]አይደለም፡፡የ ኦሮሚያ ክልል ቀደም ሲል የሸዋ ክፍለ ሀገር፣ ባሌ፣ ሐረርጌ የሚባሉትን ጨምሮ የተመሰረተ ነው፡፡ .......ወልቃይትም ሌላውም በዚህ መሠረት የተካለለ ነው፡፡ " (ሰረዝ የተደረገበት ምክንያት የአቶ ገብሩ ሀሳብ ሳይዛባ የአገላለፅ እና የአረፍተነገር አሰካክ ማስተካከያዎች ስለተደረጉበት ነዉ)።**

አቶ ገብሩ አስራት በኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ላይ ይደርስ የነመበረዉን ብሄራዊ ችቆና እስከወድያኛዉ አሽቀንጥሮ ለመጣል ከወጣትነት ዘመናቸዉ ጀምሮ ብዙ መስዋእትነት ከፍለዋል። በትግል ዘመናቸዉ ህልቁ መሳፍርት ጓዶቻቸዉን በመስዋእትነት አጥተዋል።ለአካል ጉዳት ተዳርገዋል። ቢሆንም ግን ለፍትህና ለእኩልነት የተደረገዉ ትግል ዉጤት አስገኝቷል።ከብዙዉ በጥቂቱ በብሀራዊ ጭቆና ላይ የተመሰተረዉን የቀድሞዉን አሃዳዊ አስተዳደራዊ ስርአት ለማረም አስችሏል። ይህም አቶ ገብሩን አስራትን የሚያኮራቸዉ እንጂ የሚፀፀቱበት ተግባርና ድል እንደማይሆን ተስፋ አደርጋለሁ። በ1976 በደርግ ባለስልጣኑ ፊርማ እንደተገለፀዉ የወቅቱ የወልቃይትና አካባቢዉ ነዋሪ ትግርኛ ተናጋሪ ከነበረ በሁሉም መስፈርት ወደማይመለከተዉ አካባቢ ማስፈር ለምን አስፈለገ? የሚመረጠዉና የሚቀለዉ በትግርኛ ቢተዳደር ነዉ ወይንስ በአማርኛ? ባህሉ፣ ልማዱ፣ዳኝነቱ፣ ትምህርቱ ወዘተ ይበልጥ የሚገለፀዉ፣የሚዳብረዉ እና የሚታቀበዉ በአማርኛ ነዉ ወይንስ በትግርኛ? መልሱን ለደርግ ወቅት አስተዳዳሪዎች እተወዋለሁ። ዋነኛ ዓላማዉ ግን አንድ እና አንድ ነበር። ደርግም ሆነ ቀድሞዉት የነበሩት ገዥዎች በኢትዮጵያ ዉስጥ በአንድ ቋንቋ፣ሀይማኖት፣ባህል፣ በአጠቃላይ ደግሞ በአንድ ማንነት የተጨፈለቀ ህዝብ በመፍጠር ላይ የተመሰረተ ተልእኮ ስለነበራቸዉ ነዉ።

## 4.1.3. ህዝቡ ምን ይላል?

በየደረጃዉ ባሉ የአስተዳደር መዋቅሮች የሚኖረዉ የወልቃይት ህዝብ በማንነቱ ጉዳይ ላይ ተወያይቶ የሰጠዉን አስተያየት እና ያሳለፈዉ ዉሳኔ በስፋት ተደምጧል። በየደረጃዉ ያሉ የመስተዳድር አካላት በጉዳዩ ላይ መግለጫ ሰጥተዉበታል። ህዝቡን በተከታታይ እንዳደመጥነዉ በአጭሩ "ትግራይ አይደለሁምና ከትግራይ ክልላዊ መስተዳደር ዉጭ መሄድ እፈልጋለሁ የሚል ካለ መብቱ ነዉ። ቢሆንም ግን ማንነታችንን ለድርድር አናቀርብም። ስለትግራይነታችን ሌላ መስካሪም ድምፅ ሰጪም አያስፈልገንም። በቀድሞዎቹ አምባገነን መንግስታት የተፈፀሙብን የመሸጥ ተግባር ከእንግዲህ እንዲፈፀምብን አንፈቅድም። በመሆኑም በትግላችን ያረጋገጥነዉን የማንነት ጉዳይ ታሪካዊ ጭብጥ በሌላቸዉ እና የብዙሃኑን ህዝብ ፍላጎት ግምት ዉስጥ ባላስገቡ ምክንያቶች ሰላማችንን አታዉኩት" የሚል ምላሽ ሰጥቷል። የክልሉ መስተዳድር ክቡር አቶ አባይ ወልዱ በበኩላቸዉ በዚህ ጉዳይ ላይ እስከ ቀበሌ ድረስ ባለዉ የመስተዳድር እርከን በተካሄዱ ተከታታይ ኮንፍረንሶች ህዝቡ በአንድ ድምፅ ትግራይነቱን ስለማረጋገጡ አስረግጠዉ ተናግረዋል። በቅርቡ በሰጡት መግለጫ "የወልቃይት ህዝብ በታሪክም በማንነትም ትግራይ ነዉ።ከህወሓት ጋር ተደራጅቶ ባደረገዉ ጠንካራና መራር ትግል ደርግን በመደምሰስ ብሄራዊ ማንነቱን በትግሉ ያስመለሰ ህዝብ ነዉ።በኢህአዴግ ደረጃ በተካሄደ ግምገማም ቢሆን የዚህ ህዝብ ማንነት ጉዳይ ጥያቄ ዉስጥ አልገባም። በኢህአዴግ ምክር ቤትም ሆነ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ደረጃ በተካሄደዉ ግምገማ ጥያቄዉ የኢትዮጵያን ፌዴራሊዝም ለማፍረስ የተደራጁ ትምክህተኛ ሀይሎች እንጂ የዉስጥ ጥያቄ እንዳልሆነ ግልፅ አቋም ተይዞበታል።ጉዳዩ የትግራይ ክልል፣የህወሓት እና የህዝቡ የራሱ እንጂ የሌላ ዉጫዊ አካል ጉዳይ አለመሆኑ ድምዳሜ ላይ ተደርሷል።በማንነቱ ጉዳይ ላይ ሌላ ህዝብ ወይም አካል ጥያቄ ሊያቀርብለት አይችልም።ስለሆነም ጥያቄዉ የወልቃይት ህዝብ ሳይሆን የደርግ ጥያቄ ነዉ።...."በማለት በየኮንፍረንሶቹ በህዝቡም ሆነ በኢህአዴግ ስራ አመራር ኮሚቴዎች የተላለፈዉን ዉሳኔ እና የተያዘዉን አቋም በአጽንኦት ገልፀዋል።

***"..... ማንነታችንን ለድርድር አናቀርብም። ስለትግራይነታችን ሌላ መስካሪም ድምፅ ሰጪም አያስፈልገንም። በቀድሞዎቹ አምባገነን መንግስታት የተፈፀሙብን የመሸጥ ተግባር ከእንግዲህ እንዲፈፀምብን አንፈቅድም...."***

እነዚህ ሁሉ ጥሬ ሀቆች እንደተጠበቁ ሆነዉ የወልቃይት ህዝብ የማንነት ጉዳይ በህገመንግስታዊ የአሰራር ስርአት ይፈታ ቢባል እንኳ ዉጤቱ ሳይታለም የተፈታ ነዉ። በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ህዝቡ በማንነቱ ላይ ድምፅ ይስጥ ቢባል ዉጤቱ ዞሮ ዞሮ በኮንፍረንሶችም ሆነ በህዝብና ቤቶች ቆጠራ ስለማንነቱ ከተመዘገበዉ መረጃ የተለየ አይሆንም። አንድ ህዝብ በዲሞክራሲያዊ መንገድና ያለማንም ተፅእኖ አስቀድሞ ያረጋገጠዉን ማንነት በምንም ተአምር አይቀይርም።እስከአሁን ይህን ጉዳይ የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ህገመንግስት አንቀፅ 31ን እና ሌሎች የህግ ድንጋጌዎችን መሰረት አድርጎ በጥያቄ መልክ ያቀረበ አካል የለም። ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ ዉሳኔ ሳይሰጥበት ደግሞ ጉዳዩን ወደፌዴሬሽን ምክር ቤት ማቅረብ አይቻልም። ይቅረብ ቢባል እንኳ የክልሉ መንግስትም ሆነ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ዉሳኔ የሚሰጡት በህዝብ ፍላጎትና ዲሞግራፊያዊ መረጃዎች ላይ ተመስርተዉ ነዉ። እስከአሁን የተመለከትናቸዉ ጭብጦች ደግሞ ጉዳዩ ለሁለቱም አካላት ቢቀርብ መልስ ለመስጠት የሚያስቸግር አይሆንም። እንድ ጉዳይ በሪፈረንደም ይወሰን የሚል ዉሳኔ የሚተላለፍበት የህዝብን ስሜት እና ፍላጎት፤የህዝቡን ብሄራዊ ማንነት፤የህዝቡን ብሄራዊ ቋንቋ፣ታሪካዊ ዳራ ወዘተ ከወዲሁ ለማወቅ የማያስችሉ ሁኔታዎች ሲኖሩ ብቻ ነዉ። የህዝቡ ድምፅ ምን ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ የሚያስረዱ ታሪካዊና የፍላጎት መረጃዎች በተሟሉበት ሁኔታ የህዝብ ሀብትና ጊዜ ለማባከን ሲባል ብቻ ሪፈረንደም አይካሄድም። ድምፅ የሚሰጠዉ መንግስትን በአመፅ ለማተራመስ ነዉጥ እያቀጣጠሉ ባሉ በአጎራባች ክልል

ወይም ዉጭ በሚኖሩ የቀድሞ ስርአት ናፋቂዎች ሳይሆን በትግራይ ክልል ጥያቄ በተነሳበት አካባቢ በሚኖሩት ነዉ(ጥያቄዉ አልተነሳም እንጂ)።

***"…. ጉዳዩ የትግራይ ክልል፣የህወሓት እና የህዝቡ የራሱ እንጂ የሌላ ዉጫዊ አካል ….አለመሆኑ ድምዳሜ ላይ ተደርሷል።በማንነቱ ጉዳይ ላይ ሌላ ህዝብ ወይም አካል ጥያቄ ሊያቀርብለት አይችልም።ስለሆነም ጥያቄዉ የወልቃይት ህዝብ ሳይሆን የደርግ ጥያቄ ነዉ።…."***

ጉዳዩ ከብዙሃን ህዝብ ፈቃድና ሉአላዊነት አንፃር የሚታይ ነዉ ብለናል። ከህዝብ ፈቃድ ጋር በተያያዘ ኤስ.ቢ.ሲ. በተሰኘ ራዲዮ ጣቢያ አቶ ማርሸት መርሻ የተባሉ ተናጋሪ "…የህዝብ ፈቃድ የህዝብ ፍላጎት ቢጠየቅ ኖሮ ወልቃይት ጠገዴ ወልቃይት ጠገዴ ሆኖ ነበር የሚቆየዉ ….የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ በስደት ላይ ነዉ…..ርስቱን እትብቱ የተቀበረበትን ትቶ ተገዶ ስደት ላይ ነዉ…." የሚል ሀሳብ አቅርበዋል። አቶ ማርሸት በእርግጥም ስለህዝብ ፍላጎት የሚቆረቆሩ ከሆነ ትግርኛ ተናጋሪ የሆነዉ የወልቃይ ህዝብ እ.ኤ.አ. በ1989 በተደረገዉ የአከላለል ስርአት ወደማይመለከተዉ አካባቢ እንዲካለል መደረጉን መቃወም ይኖርባቸዋል። ማረም ካለብን የመጀመሪያዉን ስህተት ነዉ። ፍርድ የሚሰጠዉ "ስህተትን በስህተት" በማረም ሳይሆን "ስህተትን በትክክል" በማረም ነዉ። ከደርግ ዉድቀት በኋላ የተወሰደዉ እርምጃም የቀድሞዉን ስህተት በማረም ላይ የተመሰረተ ነዉ። በትምክህተኞቹ በአፄ ሚኒሊክ እና በአፄ ሀይለስላሴ አገዛዝ ስርአቶች የተፈፀሙትን ትተን ይህ ህዝብ ከፍላጎቱና ከፈቃዱ ዉጭ ይበልጥ ከሚዛመደዉ ባህል፣ ቋንቋ እና አሰፋፈር ይበልጥ ወደማይዛመደዉ እንዲሰደድ ተፈርዶበት ነበር። እዉነቱን እንነጋገር ከተባለ ስደቱ የተፈፀመ በኢህአዴግ ዘመን ሳይሆን በአንባገነኑ የደርግ ስርአት እና ከዚያ በፊት በነበሩት ገዥ መደቦች አማካኝነት ነዉ። በሽግግሩ መንግስትም ሆነ የኢፌዴሪ ህገመንግስት ከወጣ ከ1987 ወዲህ የተረጋገጠዉ ጉዳይ የህዝብ ፍላጎት ወደነበረበት እንዲመለስ ማድረግ ነዉ። ከደርግ መንግስት ጀምሮ የተከናወኑት የህዝብ ቆጠራ ዉጤቶች የሚያሳዩትም ለጥቂቶች ጥቅም ወይም ብዙሃኑን ለማጥፋት ሲባል የተፈፀሙ አስተዳደራዊ መዋቅሮችና በደሎች ናቸዉ። መከራከሪያችን ፍትሃዊነት እና የብዙሃን ፈቃደኝነት መርህ ከሆነ ቀዳሚዉ ጥፋት መታረም አለበት።የቀድሞ ስርአቶች በትግራይ ህዝብና ሌሎች ብሄረሰቦች ላይ በነበራቸዉ ጥላቻ ምክንያት የወልቃይት ህዝብ እንደሌሎቹ ሁሉ በጭቆና ላይ የተመሰረተ አስተዳደራዊ ቅጣት ተፈፅሞበታል።በሁሉም መለኪያዎች ይበልጥ ከሚዛመደዉ አካባቢ አፈናቅለዉ ይበልጥ ወደማይዛመደዉ አካባቢ እንዲሰደድ አድረገዋል። አቶ ማርሸት እና ተከታዮቻቸዉ በእርግጥም ማዉገዝ ካለባቸዉ ይህን በጥላቻ ላይ የተመሰረተ ተግባር ነዉ። ተከባብረን ልንኖር የምንችለ እና የአንድን ብሄር ጥቃት በሁላችንም ላይ እንደተፈፀመ ቆጥረን በጋራ ልንታገለዉ የምንችለዉ ፍትሃዊ መሆን እስከቻልን ድረስ ብቻ ነዉ።ያለበለዚያ ስለፍትሃዊነት እና ስለ ብዙሃን ሉኣላዊነትና ይሁንታ ስንደሰኩር ዉለን ብናድር የሚያደምጠን አይኖርም። አቶ ማርሸት! ወልቃይት በአማራ ክልል ዉስጥ ቢሆን እና በህዝብ ቤቶች ቆጠራ መሰረት ከነዋሪዉ ዉስጥ 97% አማራ 3 % ትግራይ ቢሆን እና ከአማራ ክልል ዉጭ ያሉ ትግሬዎች በስሜት እና በትምክህት ተነሳስተዉ ለ3%ቱ ሲባል ወደትግራይ ክልል ይካለል ማንነቱም ትግራይ በመሆኑ በትግርኛ ቋንቋ ይተዳደር ወዘተ የሚል ፍትሃዊ ያልሆነ ጥያቄ አንስተዉ ለነዉጥ ቢጋበዙ ድጋፎን ይሰጡ ነበር?! አቶ

ማርሸት ከፍ ብሎ በ1976 ዓ.ም. በኢሰፓ ባለስልጣኑ የተፈረመበት ድብዳቤ የሚነግረን እኮ ቀድሞዉንም እንዲሰደድ የተደረገዉ *"....ህዝቡም ትግርኛ ተናጋሪ በመሆኑ..."* የተባለለት የትግራይ ህዝብ እንጂ የአማራ ህዝብ አይደለም!

# 4.2 የድንበር ጉዳይ

በየትኛዉም ወቅት በክልሎችም ሆነ በአገሮች መካከል የድንበር አለመግባባቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ፈረንጆቹ "conflict is inevitable" እንደሚሉት ይህች ዓለም ካለመግባባቶች የፀዳች ልትሆን አትችልም። ቁምነገሩ መሆን ያለበት አለመግባባቶች ወደግጭት ከማምራታቸዉ በፊት የሚፈቱበትን ስርአት ማበጀትና በአግባቡ ስራ ላይ ማዋል ነዉ። የኢትዮጵ ህዝብ፣ መንግስትና ኢህአዴግ ደግሞ የዚህ ድህነት የለባቸዉም። እስከተገበርነዉ ድረስ ከባህላዊዉ የአፈታት ስርአት ጀምሮ ተቋማዊና ህጋዊ ስልቶቹም ሆነ ስርአቶቹ ያሉና የነበሩ ናቸዉ።እስከተጠቀምንበት ድረስ በኢህአዴግ የሚመራዉ መንግስት በዚህ አይታማም።ህገመንግስቱ አንዱ ነዉ።ምክር ቤት ሌላዉ ነዉ።የህገመንግስት አጣሪ ጉባኤም ከእነዚሁ የመነጨ ነዉ። የራስን እድል በራስ የመወሰን እና የድንበር ዉዝግብ አፈታትን ጭምር የሚያስረዱን ህግጋትም ጥቅም ላይ ሊዉሉ የሚገባቸዉ ናቸዉ።የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብትን ጨምሮ ግጭትን በመከላከል እና በመፍታት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያላቸዉን ሌሎች የዲሞክራሲ ተቋማትንና ህግጋትንም መዘርዘር ይቻላል።

በሚመለከተዉ ህዝብና ለሚመለከተዉ አካል በግልፅና ህጋዊ ስርአትን ተከትሎ ባለመቅረቡ ጥያቄዉ የድንበር ይሁን የማንነት ጉዳይ ለብዙዎቻችን ግልፅ ባይሆንም የድንበር ጉዳይንም እንደምክንያት አቅርበን ብንመለከተዉ አይከፋም። በዚህ ረገድ ተደጋግመዉ የሚነሱት አዋሳኝ ወረዳዎች በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በኩል ጠገዴ በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በኩል ደግሞ ፀገዴ የሚባሉት ናቸዉ። እ.ኤ.አ በ2007 በተካሄደዉ የህዝብና ቤቶች ቆጠራ መሰረት በጠገዴ ወረዳ 73 898 ፤በፀገዴ ወረዳ ደግሞ 103852 ይኖር እንደነበር ሪፖርቱ ያመለከትታል። ሁለቱም ወረዳዎች በሞላ የይገባኛል ጥያቄ ተነስቶባቸዋል ብለን ብናስብ እንኳ መፍትሄዉ ያን ያህል የሚያስቸግር አይሆንም። ጉዳዩ ወደህዝበ ዉሳኔ ሳያመራ በሁለቱም ወረዳዎች የሚኖረዉ ህዝብ ዲሞግራፊያዊ ዳራ አንዱ የመወሰኛ መስፈርት ነዉ። ለምሳሌ በጠገዴ ከሚኖረዉ 73 898 ህዝብ ዉስጥ በቆጠራ ወቅት ትግርኛ ተናጋሪነቱን የተረጋገጠዉ 10% ብቻ ቢሆን አሰፋፈርንና ቋንቋን መሰረት በሚያደርገዉ የአከላለል ስርአታችን መሰረት የወረዳዉ ህዝብ የመኖሪያ አካባቢዉ ወደ ትግራይ ክልል እንዲተላለፍ ይመርጣል ተብሎ ሊታሰብ አይችልም። በተመሳሳይ ሁኔታ በፀገዴ ከሚኖረዉ 103852 ህዝብ ዉስጥ ትግርኛ ተናጋሪዉ ከ88% በላይ ከሆነ የመኖሪያ አካባቢህን ምረጥ ቢባል የብዙሃኑ ምርጫ ወደአማራ ክልል ይሆናል ተብሎ አይታሰብም። ለምሳሌ በ1987 በተካሄደዉ ቆጠራ በፀገዴ ወረዳ(ትግራይ ክልል) ከሚኖረዉ 59846 ህዝብ ዉስጥ 45 532 ትግራይ፤14226 አማራ ስለመሆኑ ተወስቷል። ከዚህ አኳያ የህዝቡን የመኖሪያ አካባቢ ለመወሰን ህዝበዉሳኔ ማካሄድ ይግድ አይሆንም። የአከላለል ስርአታችን የብዙሃንን ፍላጎትና ይሁንታ ማእከል ያደረገ በመሆኑ 45532 ህዝብ ፍላጎት በ14226 ፍላጎት ተቀይሮ የትግራዩ ፀገዴ ወደአማራዉ ጠገዴ ይካለል ሊባል አይችልም። እነዲህ አይነት ፍትህ የጎደለዉ የህዝብ አሰፋፈር ስርአት የምንከተል ከሆነ ከህገመንግስታችን አንቀፅ 39 ጀምሮ በየህግጋቱ ያሰፈርናቸዉን የራስን እድል በራስ የመወሰን መርሆዎች መጣረስ ይሆናል። ጥያቄዉ በእነዚህ ወረዳዎች ዉስጥ ያሉ አዋሳኝ ቀበሌዎችን ብቻ የሚመለከት ቢሆንም እንኳ መፍትሔዉ ይኸዉ የብዙሃን ህዝብ ሉኣላዊነት መርህ ነዉ። የክልል መስተዳድሮቹ በአዋሳኝ ቀበሌዎቹ ያለዉን የብሄር ብዛት እና ታሪካዊ መረጃዎች መሰረት አድርገዉ በእርግጥም የህዝቡ መኖሪያ አካባቢ ምርጫ ወደየትኛዉ እንደሆነ ማወቅ ይችላሉ።ማወቅ ይችላሉ ብቻ ሳይሆን ህዝባዊ ኮንፍረንሶችን በማካሄድ

ከብዙሃን ሉአላዊነትና ፍላጎት የተለየ አካሄድ ፀረዲሞክራሲያዊነት መሆኑን ሊተማመኑበት ይችላሉ። ይህን መንገድ ተጠቅመዉ ከህዝባቸዉ ጋር እስከተማመኑ ድረስ በግጭትና በጥላቻ ላይ የተመሰረተ የመጠፋፋት መርህ ይቅርና በሰላማዊ መንገድ የሚካሄደዉ የሪፈረንደም አፈታት ስርአትም ላያስፈልግ ይችላል። ምክንያቱም ብዙዉን ጊዜ ሪፈረንደም የሚካሄደዉ የህዝብን ፍላጎት ከወዲሁ ለመለየት አስቸጋሪ ሲሆን ነዉ። ሌላዉ ደግሞ ለምሳሌ በትግራዩ ፀገዴ ወረዳ የሚኖረዉ አማራነቱን ያረጋገጠዉ ህዝብ ከ50% በላይ ቢሆን የቀድሞዉ የአከላለል ስርአት ጥርጣሬ ዉስጥ ሊገባ ይችላል። ቀድሞዉንም የብዙሃኑ ህዝብ ፍላጎት እንዳልተጤነ የሚያመለክት ቁጥር በመሆኑ ህዝቡ የራሱን እድል በሪፈረንደም ይወስን ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርስ ይችላል። ይህም ቢሆን "...ታጠቅ ተነሳ የቋራዉ አንበሳ..." የሚል የእርስ በእርስ ግጭትን ሊጋብዝ አይገባዉም። ሁሉም ችግሮች ደረጃ በደረጃ የሚፈቱበትን ስርአት እስካስቀመጥን ድረስ ያንኑ ብቻ መጠቀም ነዉ። ሌላዉ መንገድ ከጥፋት ያለፈ ሰባራ ሳንቲም አያስገኝም። ሰላምና አንድነታችንን ከማተረማመስ ያለፈ ፋይዳ አይኖረዉም።

## *ህዝብ ጥያቄ አለኝ ካለ መንቀሳቀስ ያለበት በራሱ ዛቢያ ዙሪያ እንጂ የሌሎች ህዝቦችን የራስን እድል በራስ የማስተዳደር መብት በሀይል በሚጥስ መንገድ ሊሆን አይገባዉም*

በዚህ ረገድ ጥያቄ አለኝ የሚል ካለ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መመንገስት ህገመንግስት አንቀፅ 30 መሰረትም ሆነ ሌሎች ደጋፊ ድንጋጌዎችና ህግጋት መሰረት በህጋዊ እና በሰላማዊ መንገድ ለሚመለከተዉ አካል ማቅረብ ይችላል። በትግራይ ወገን የሚቀርብ ጥያቄም ካለ የክልሉን ህገመንገስት አንቀፅ 31ንም ሆነ ሌሎች ህግጋትንና ድንጋጌዎችን መሰረት አድርጎ ማቅረብ ይቻላል። ሁሉም ጉዳዮች በህጋዊና ሰላማዊ መንገድ ከቀረቡ የማይታዮበት እና ተገቢዉ ምላሽ የማይሰጥበት ምንም ምክንያት አይኖርም። ጥያቄዉ ህዝብ ሳይሆን ህዝቡን የሚወክሉት የመስተዳድር አካላት እና መሪ ድርጅቶች ቢሆንም እንኳ በተሰጣቸዉ ስልጣንና ሀላፊነት መሰረት አንዱ ክልል ለሌላኛዉ ማቅረብ እና መወያየት ይችላሉ። እኛ የማናዉቀዉ የዉስጥ ችግር ከሌለባቸዉ በስተቀር ለግጭትና ሁከት እስኪጋብዝ ድረስ መጠበቅ የለባቸዉም።ቀድሞ የምናዉቀዉን ችግሮችን በዉይይት የመፍታት ባህል ያዳበረዉን ኢህአዴግ የሚዉክ ዉስጣዊ ችግር ካለባቸዉም በቅድሚያ ዉስጣቸዉን ማጥራት ይኖርባቸዋል። ለማንኛዉም ግን የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት አንቀጽ 39 ንኡስ አንቀጽ 2 የክልሉ ህዝብ መብቶች "በራሱ መልክአምድራዊ ክልል ዉስጥ የራሱን ጉዳይ በራሱ የመጨረስ ራሱን በራሱ የማስተዳደር...." መብት እንዳለዉ ይደነግጋል። የትግራይ ህገመንግስትም ተመሳሳይ ድንጋጌ አስፍሯል። በመሆኑም ህዝብ ጥያቄ አለኝ ካለ መንቀሳቀስ ያለበት በራሱ ዛቢያ ዙሪያ እንጂ የሌሎች ህዝቦችን የራስን እድል በራስ የማስተዳደር መብት በሀይል በሚጥስ መንገድ ሊሆን አይገባዉም። በበሄር ላይም ሆነኔአማራ ህዝብ ጥሮ ግሮ ባፈራዉ ሀብትና ንብረት ላይ ያነጣጠረ ጥቃትና ዉድመት ከማድረስ ይልቅ አቤቱታ አቀራረብ ስርአቶችን ተጠቅሞ ማቅረብ ስልጣኔ እንጂ ኋላቀርነት ወይንም ዉርደት አይደለም።

*ዘመኑ የስልጣኔ ነዉ። መፍትሄዉም እንደዚያዉ። እዉነቱን እንነጋገር ከተባለ ኢትዮጵያዊን ስለራሳችን የምንሰጠዉ ቦታ እና ሆነን የምንገኘዉ ሰማይና ምድር ነዉ። ስለራሳችን ስልጣኔ ስናወራ የሚደርስብን የለም። ለስነምግባርና ለሞራል ያለንን ተገዥነት በተመለከተም ከኛ በላይ ላሳር የምንል ህዝቦች ነን። ስለህዝብ አክባሪነታችን ስናወራ በዓለም ላይ ተወዳዳሪ የለንም። በተግባር ስንመዘን ግን በቦታዉ ከማይገኙት ቀዳሚዎቹ*

***እኛ ነን። "ኢትዮጵያዊያን ጨዋዎች ናቸዉ" የሚል ታርጋ ተለጥፎልናል። በተግባር ግን ጨዋነት አጠገባችን አይደርስም። ጨዋ ህዝብ በራሱ ሀብትና ጉልበት የተገነባን ለዘመናት ተደከመበትን ይቅር እና የሌሎች ወገኖችን ሀብትና ንብረትም አያወድምም። ህግና ስርአት እያለ የገዛ ወገኖቹን ለስደትና ለእንግልት አይዳርግም። ለስነምግባርና ለሞራል ግዴታ ተገዥ የሆነ ህዝብ የዜጎችን ህይወት ለማጥፋት ነዉጥ አያስነሳም። በድሃዉ ህዝብ ሀብት የተገነቡ ተቋማትን አያወድምም። ህዝብን የሚያከብር ወገኖቹን አይገድልም። ለአገሩና ለህዝቡ እድገት ቁልፍ መንገድ የሆነዉን ሰላማዊ የአፈታት ስልት በማጣጣል ህዝቡን ለችግርና ለእንግልት የሚዳርግ መንገድ አይመርጥም። ስልጣኔ ማለት ከዚህ አንፃር የሚመዘን ነዉ። በአዉሮፓና በአሜሪካ ተቀምጠን መሰልጠን ካልቻልንና ህዝባችን ችግሮቹን በተቀመጡለት የአፈታት ስልቶች እንዲፈታ አርአያ ካልሆን በባህር ዉስጥ እንደኖረ አለት ማለት ነን። በዉሃ ዉስጥ የሚኖር አለት የዉሃ ፍሰት በላዩ ላይ ሲፈራረቅበት ቢኖርም ምንም አይነት ለዉጥ አያሳይም። ዋነኛዉ ደደብ ሰብእና ደግሞ ትምህርት ቤት ገብቶ የአስተሳሰብና የአመለካከት ለዉጥ ያላመጣዉ ሳይሆን በስልጣኔ ዉስጥ ኖሮና በዚያዉ ስርአት ተገዝቶ መለወጥ ያልቻለዉ ነዉ። በተግባር ኖረንበት ካልተለወጥን ከድንጋይም ድንጋይ ነን። አንዳንድ የአዉሮፓና የአሜሪካዩፖለቲካ አስተሳሰቦች ለእድገቷ የምትተጋና ከጥገኝነት የተላቀቀች አፍሪካና ማየት እንደማይፈልጉ ጠንቅቀን የምናዉቀዉ ጉዳይ ነዉ። የራሳችንን እና የቤተሰባችንን ሆድ እስከምሉልን ድረስ ለድህነታችን እና ለሰላም እጦታችን ምክንያት የሆነዉ የእነርሱ ርእዮተዓለም እሳት እየተቀጣጠለ እንዲኖር በማረገብገቢያነት ብቻ የምናገለግል ከሆነ ምኑ ላይ ነዉ ጨዋነታችንና ህዝብና ሀገር መዉደዳችን? ጨዋነት እና ሀገር ወዳድነት እኮ ለህዝብና ለአገር ጥቅም በሚኖረን አስተዋፅኦ የሚመዘን ነዉ! ከኢትዮጵያ ዉጭ ሆነዉ ግፉ በለዉ ለሚሉት ፕሮፌሰር ይሁን ዶ/ር ተብየዎች እና ሰላማዊዉን የኢህአዴግ ስርአት አብጠልጣዮች ይመለከታል። የአገር ዉስጥ ተከታዮቻቸዉም ቢሆኑ ከዚህ ትችት የሚታደጋቸዉ እይኖርም።***

የኢህአዴግ የተሃድሶ መስመር እንደሚያስረዳን መስራች ብሄራዊ ድርጅቶቹ በዉስጣቸዉም ሆነ በመካከላቸዉ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች፣ጥያቄዎች እና ችግሮች ቢኖሩ እንደየጉዳዩ ሁኔታ አስፈላጊ በሆነዉ መድረክ እና ስርአት መፍትሄ የመስጠት ባህላቸዉ የዳበረ ነዉ። ኢህአዴግ የዉስጥ ችግሩን ይቅርና የሌሎች አግሮችን ግጭቶችና አለመግባባቶች በመፍታት ረገድ ዓለምአቀፍ እዉቅናን ያተረፈ መሪ ድርጅት ነዉ። የኢትዮጵያ መንግስት ለምሳሌ የደቡብ ሱዳንን፣የሁለቱን ሱዳኖች፣ የሶማሊያን እና የሌሎች አገሮችን በመፍታት ሂደት ቀዳሚ ሚና እንዲጫወት ለምርጫ ያበቁት ምክንያቶች መንግስትን ከፊትና ከኋላ ሆኖ አቅጣጫ የሚያሲዘዉ የፖለቲካ ድርጅት(ኢህአዴግ) ጠንካራ የመሆን ጉዳይ ነዉ። በዚህ ረገድ በቅርቡ በኢህአዴግ ደረጃም ሆነ

በሁለቱ የፖለቲካ ድርጅቶች እና ክልላዊ መንግስታት ደረጃ ችግሩን ለመፍታት እየተወሰዱ ያሉት እርምጃዎች እና የተሰጡት መግለጫዎች የሚበረታቱ ናቸዉ። ወደይዘታቸዉ ከመግባታችን በፊት ግን በተለይ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በተነሱት ነዉጦች ሳቢያ በደርግ አስተሳሰብ ተሸካሚዎች አማካኝነት የዘር ማጽዳት እስኪመስል ድረስ በብሄር ላይ ያነጣጠሩ ተግባራት መፈፀም በተጀመሩበት ጊዜ በመንግስትም ሆነ በብአዴን ደረጃ ፈጣን የሆኑ የማዉገዝ እርምጃዎች አልተወሰዱም። ቀደም ሲል ከሚመለከታቸዉ የክልሉ መንግስት ባለስልጣናት የተሰጡት መግለጫዎች ለዘብተኛ በመሆናቸዉ ለነዉጠኞቹ የልብ ልብን ሰጥተዋል የሚል እምነት አሳድሯል-በዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ግምገማ። በወቅቱ ያደመጥናቸዉ ንግግሮች ኢህአዴግ በቅርቡ ሁኔታዉን ገምግሞ ዉሳኔ ካስተላለፈ በኋላ የተለዩ እና ነዉጠኞቹ የልብ ልብ እንዲሰማቸዉ የሚዳርጉ ነበሩ። ያ ባይሆን ኖሮ በአማራ ክልል ህዝብ ሀብት እና ንብረት ላይም ሆነ በብሄረሰብ ላይ አነጣጥሮ በተወሰዱ እርምጃዎች በዚ ጉዳት ባልደረሰ ነበር። የቅርቡ የኢህአዴግ ግምገማም ይህንን ግምት ዉስጥ ያስገባ ይመስለናል። ለማንኛዉም ጉዳዩን ወደተለመደዉና ወደሰለጠነዉ የችግር አፈታት መስመራችን አስገብተነዋል። በዚህ ተገድ የክልሉ ፕሬዚደንት ክቡር አቶ ገዱ አንዳርጋቸዉ በቅርቡ ያቀረቡትን ሀሳብ መሰረት አድርገን ስለድንበር ጥያቄዉ ጉዳይ የበኩላችንን እንበል። እንዲህ ብለዋል፦

“**1.**<u>የጠገዴንና ፀገዴን ድንበር ሁለቱ ክልሎች ተነጋግረው በአጭር ጊዜ ውስጥ</u> መፍትሄ ይሰጣሉ፡፡
*<u>2.የወልቃይት ማንነት ጥያቄም በትግራይ ክልል ቀርቦ ምላሽ ያገኛል፡፡</u>*
*<u>3.በጐንደር የሚኖሩ የወልቃይት ኗሪዎች ጥያቄቸውን በሰለማዊ ሁኔታ የማቅረብ መብት [አላቸዉ]</u>*(ሰረዝ የተጨመረበት)።....
የወልቃይት ኗሪዎች ጥያቄያቸውን ለትግራይ ክልል አቅርበው ምላሽ ያገኛሉ፡፡”

ከዚህ በላይ በተጠቀሰዉ ሀሳብ ዉስጥ ሰረዝ የተደገበትን መመልከቱ ጥሩ ነዉ። ሁለቱን ክልሎች በተለይ ሊያነጋግር የሚችለዉ ጉዳይ በክልሎቹ አዋሳኝ አካባቢዎች የመኖሪያ አካባቢን ለመለወጥ የሚነሳ ፍላጎት ካለ ነዉ። ይኸዉም በተራ ቁጥር 1 የተጠቀሰዉን ሀሳብ የሚመለከት ነዉ። የማንነት ጥያቄ ከሆነ ግን ጥያቄ አቅራቢዉም መፍትሄ ሰጪዉም ጥያቄ በተነሳበት አካባቢ የሚኖረዉ ህዝብ እና የክልል መስተዳድር ነዉ። ይህም በተራ ቁጥር 2 የተጠቀሰዉን ይመለከታል። በተራ ቁጥር 3 የተጠቀሰዉ ግን የመኖሪያ አካባቢን ስለመወሰን ይሁን የማንነት ጥያቄን በግልፅ አላስቀመጠም። ጉዳዩ ድንበርን የሚመለከት ነዉ እንዳንል የድንበር ዉዝግቡ በጠገዴ እና ፀገዴ ወረዳች ያለ አካባቢን ብቻ እንደሚመለከት እየተነገረን ነዉ። ይህ ሀሳብ ማንነትን የሚመለከት ነዉ እንዳንል የወልቃይት ህዝብ የማንነት ጥያቄ ለትግራይ ክልል ቀርቦ መልስ እንደሚያገኝ ተነግሮናል። ስለዚህ “....<u>*በጐንደር የሚኖሩ የወልቃይት ኗሪዎች ጥያቄቸውን በሰለማዊ ሁኔታ የማቅረብ መብት [አላቸዉ]...”*</u> ሲባል በጎንደር ዉስጥ እየኖሩ በትግራይ ዉስጥ ስለሚኖረዉ የወልቃይት ህዝብ ማንነት ጉዳይ ጥያቄ እያቀረቡ ነዉ? ጥያቄአቸዉ የማንነት ጉዳይ ከሆነስ ለማን ነዉየሚያቀርቡት? ጉዳዩ የማንነት ከሆነና በአማራ ክልል ዉስጥ እየኖሩ ጥያቄአቸዉን የሚያቀርቡት ለአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ከሆነ “እኛ አማሮች ሳንሆን ትግራዮች ነን” የሚል ጥያቄ ነዉ የሚያቀርቡት? ሀሳቡ ግልፅ ስላልሆነ አንድም ከድንበር አለያም ከማንነት ጥያቄ አፈታት አንፃር አቋም ይዞ አስተያየት ማቅረብ አላስቻለም። ለማንኛዉም ጥያቄአቸዉ የመኖሪያ አካባቢን የመወሰን ጉዳይ ከሆኖ አሁንም ቢሆን እየኖሩ ያሉት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ስር ነዉ። ምንልባት እንደጥያቄ ሊሆን የሚችለዉ ከትግራይ ጋር በሚያዋስነዉ በጎንደር የሚኖሩ ህዝቦች በአሰፋፈር፣ በቋንቋና በሌሎች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት መስፈርቶች ከአማራ ክልል ይልቅ ወደትግራይ ክልል መካተት አለብን የሚል አቤቱታ ካቀረቡ ነዉ። ይህ መብታቸዉ ሊስተናገድ ይችላል። ወሳኙ ግን (ከፍ ብሎ እንደተገለፀዉ) ጥያቄ በሚቀርብባቸዉ አዋሳኝ አካባቢዎች ያለዉ ብዙሃን ህዝብ ፍላጎት ነዉ። በዚህም ጉዳይ የሚከበረዉና የሚደመጠዉ የብዙሃን ሉኣላዊነት መስፈርት ነዉ። የሆኖ ሆኖ ሁሉም

አይነት መብቶችና ጥያቄዎች ቢቀርቡ ለኢህአዴጋዊያን ትልቅ ራስ ምታት አይደሉም። የችግር መፍቻ ተቋማቱም ሆኑ ህግጋቱ ከፊት ለፊታችን አሉ። ከመንግስታትና ከህዝብ የሚጠበቀዉ እነዚህን መፍቻ ስርአቶች በአግባቡና በዲሞክራሲያዊ መንገድ ብቻ መጠቀም ነዉ። የራሳችንን ህግጋትና የመፍቻ ስርአቶች ሳናከብር ስለዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ኢንስትሩመንቶች እና የሌሎች አገሮች የዲሞክራሲ ስርአቶች እየተደነቅን ብንደሰኩር በተግባር የሚሰጠን ነጥብ ዜሮ ነዉ። በጎንደር እና በሌሎች የአማራ አካባቢዎች የታየዉ ክስተት በኛ በተግባር ዜሮ ነጥብ ያገኘንበት ስለሆነ መሻሻል ይጠበቅበታል።

# 4.3 ጥያቄዉ ምንም ይሁን ምን?

ሀ.ተደጋግሞ እነደተገለፀዉ በሁለቱም መንግስታት እና ክልሎች መካከል ታይቶ ሊፈታ የማይችል ጉዳይ ካለ ቀጣዩ ምእራፍ የህገመንግስታችንን አንቀፅ 48 እና ይህን መሰረት አድርገዉ የወጡ ህግጋትን መጠቀም ነዉ። በዚህ አንቀፅ መሰረት የፌዴሬሽን ም/ቤት ጉዳዩ በቀረበለት ከ 2 ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ዉስጥ ከዲሞግራፊ፣ ከአስተዳደራዊ እና ህገመንግስታዊ ይዘቶች አንፃር ተመልክቶ ምላሽ ይሰጥበታል። ሆኖም ግን የድንበር ጥያቄ የሚያቀርበዉ መሪ ድርጅትና የክልል መስተዳድር የጥያቄዉን አግባብነት በቅጡ ካልመዘነዉ ግምት ዉስጥ ሊጥለዉ ይችላል። መንግስትና የጎዳና ላይ ነዉጠኞች ጥያቄች ተመሳሳይ ሰብእና ሊኖራቸዉ አይገባም። ከአዋጅ ቁጥር 7/1992 ጀምሮ ያሉት ህግጋት ይታያሉ።ብሄር ብሄረሰቦችን በመከፋፈል ህልዉናቸዉን ለማጥፋት ዓልመዉ የተከናወኑት የአሰፋፍርና የአስተዳደር ስርአቶች ግምት ዉስጥ ይገባሉ።የቀድሞ ስርአቶች መረጃዎች ጥቅም ላይ ይዉላሉ። ለምሳሌ በደርግ ጊዜ በወጣዉ መግለጫ ዉስጥ "…በወልቃይትና በጠገዴ ወረዳዎች ነፃ እንቅስቃሴ የማድረግ እድል ስላገኘ ህዝቡም ትግርኛ ተናጋሪ በመሆኑ…." የሚለዉ የወልቃይት ህዝብ ብቻ ሳይሆን ጠገዴ እና ፀገዴ በተሰኙት የሁቱም ክልሎች ወረዳዎች ይኖር የነበረዉ ህዝብ(የወቅቱ ጠገዴ ወረዳ) ትግርኛ ተናጋሪ እንደነበር ይጠቁመናል።

ለ.የፌዴሬሽን ም/ቤትን ለማጠናከር እና ስልጣንና ተግባርን ለመዘርዘር የወጣዉን አዋጅ ቁጥር 251/1993 አስፈላጊ ድንጋግዎች ስራ ላይ ይዉላሉ። በዚህ አዋጅ መሰረት "…ማንነቴ ይታወቅልኝ…" የሚል ጥያቄ የራስን እድል በራስ የመወሰን ጉዳይ እንደሆነ ተደንግጓል። በአዋጁ አንቀፅ 20 መሰረት የማንነትም ይሁን የድንበር ጉዳይ ጥያቄዎች ለፌዴሬሽን ም/ቤት ከመቅረባቸዉ በፊት በቅድሚያ ህዝቡ በሚኖርበት ክልል የሚሰጡ መፍትሄዎች ተሟጠዉ መታየት እና ጥያቄ አቅራቢዎችም ይህን የመተግበር ግዴታ እንዳለባቸዉ ተደንግጓል። የክልሉ አስተዳደርም ጥያቄዉ በቀረበለት በ2 ዓምት ጊዜ ዉስጥ ተገቢዉን ምላሽ መስጠት ይኖርበታል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ጥያቄዉ የነዋሪዉ ህዝብ ወይም የብሄር ብሄረሰቡ መሆኑን ለማመልከት እንደአስፈላጊነቱ ከነዋሪዉ ወይም ከብሄር ብሄረሰቡ መካከል ቢያንስ በ5% ስም ዝርዝርና ፊርማ ወይም በጥያቄ አቅራቢዉ መስተዳድር አካል ተፈርሞ እና መሃተም ተደርጎበት መቅረብ ይኖርበታል።ከዚህ አኳያ በተለይ በትግራይ ክልል ያለዉ የወልቃይት እና የፀገዴ ህዝብ ወይም

የአካባቢዉ አስተዳደር ለትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት እስከአሁን ያቀረበዉ ጥያቄ የለም። በየትኛዉም አካል ከማንነትም ሆነ ከድንበር ጋር ተያይዞ የቀረበ ጥያቄ አለመኖሩን የክልሉ ርእሰ መስተዳድር ክቡር አቶ አባይ ወልዱ ከሰጡት መግለጫ ማረጋገጥ ተችሏል። የሙብት ጥሰትም እንዲታረም፣ የማንነትም ሆነ የይገባኛል ጥያቄ እንዲከበር ጥያቄ ማቅረብ የግድ ነዉ። ጥያቄ ባልቀረበበት ሁኔታ ስለሰብአዊም ሆነ ዲሞክራሲያዊ ሙብት ጥሰት መናገር አይቻልም። ስርአቱን ጠብቆ ጥያቄ ባልቀረበበት ሁኔታ ለሰላማዊ ስልፍም ሆነ ለነዉጥ የሚያስገድድ ጉዳይ አይኖርም።

ሐ.በአዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀፅ 24 መሰረት የሁለቱም ክልሎች መንግስታት በድንበርም ሆነ በሌላ ጉዳይ ላይ የተመሰረተ የዉይይት ጥያቄ ሲቀርብላቸዉ በቅን ልቦና ተቀብሎ ማስተናገድ ይጠበቅባቸዋል።ይህን ጉዳይ ከትግራይ ክልል አንጻር ስንመለከተዉ ህገመንግስታዊ ስርአቱን እና ሌሎች ህግጋትን ተከትለዉ የቀረቡ ጥያቄዎች የሉም። ከዚህ ይልቅ በሌሎች ክልሎች እና ከሀገር ዉጭ ሆነዉ ሲደረጉ በነበሩት የነዉጥ ዘመቻዎች ምክንያት ህዝቡ ከላይ እስከታች ባሉት የአስተዳደር እርከኖች እንዲወያይበት የሚያስችል ተከታታይ ኮንፍረንሶች ተካሂደዋል።ህዝቡ በማንነቱም ሆነ የመኖሪያ አካባቢዉን በመወሰን ጉዳይ ላይ ግልፅና የማያዳግም አቋም መያዙን ክቡር ፕሬዚደንቱ ገልዋል። ስለሆነም ክልሉ ስርአቱን የጠበቀ ጥያቄ ባይቀርብለትም እንድ እርምጃ ወደፊት ሄዶ ህዝቡን አወያይቷል። በመሆኑም የክልሉ መንግስት ጉዳዩን ከቅን ልቦና በላይ ተጉዞ አስተናግዶታል። ከዚህ በተረፈ በገሃድ እየታየ ያለዉ ሀይል የተቀላቀለበት እርምጃ ይሁንታዉን ወዳልሰጠበት የመኖሪያ አካባቢ እንዲቀላቀል ሲተላለፍበት የኖረዉን ተፅእኖ በመድገም ላይ ያነጣጠረ ፀረ ህገመንግስታዊነት ነዉ። ይህ ህዝብ ከቀዳማይ ወያኔ ዘመን ጀምሮ ለማንነቱና ለአሰፋፈር ሙብቱ ባደረገዉ ተጋድሎ ድሉን በደርግ ዉድቀት ተጎናጽፏል። ሪፈረንደም ቢካሄድ እንኳ ይህን ድል በምርጫ ካርዱ አሳልፎ ይሰጣል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነዉ።

በሁለቱ ክልሎች መካከል ለዉይይት የሚጋብዝ ጥያቄ ኖሮ መግባባት ላይ ባይደረስበትና ለፌዴሬሽን ም/ቤት እንዲመራ ቢደረግ እንኳ ችግሩ የሚፈታዉ በአዋጅ ቁጥር 251 አንቀፅ 29 እና 30 መሰረት ነዉ። በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት የህዝብ ፍላጎት የሚረጋገጠዉ ዉዝግብ በተነሳበት አስተዳደራዊ አካባቢ ባለዉ ነዋሪ በሚሰጠዉ ድምፅ ነዉ። ከዚያ በፊት ግን ምክር ቤቱ በአንቀፅ 28(1) መሰረት አሰፋፈርን መሰረት አድርጎ ዉሳኔ ሊያሳልፍ ይችላል። ይህን ለመወሰን የሚያስችል ታሪካዊም ሆነ ሌሎች ዲሞግራፊያዊ መረጃዎች ከፊት ለፊቱ እንደሚቀርቡ ከወዲሁ ማረጋገጥ ይቻላል። ለምሳሌ ያህል በህዝበ ዉሳኔ ብዙሃን ድምፅ ተደርጎ የሚወሰደዉ ከድምፅ ሰጪዉ አብዛኛዉ የቀረበዉን ጥያቄ ከደገፈ ነዉ። በተከታታይ የተከናወነዉ የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ዉጤት የሚያመለክተዉ ደግሞ በተለይ በትግራይ ክልል ባሉት የወልቃይት እና ፀገዴ አካባቢ ነዋሪዎች በአማካይ ከ88% በላይ የሚሆነዉ ትግራይነቱን አረጋግጧል። ብዙሃኑ ነዋሪ በሌላ አካባቢዎች ከሚኖረዉ የትግራይ ህዝብ ጋር ተመሳሳይ ባህል፣ልማድ፣ ቋንቋ፣ የተዛመደ ህልዉና ያለዉ መሆኑን ከወዲሁ አረጋግጧል። ስለሆነም የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጥያቄዉ በድንበርም ሆነ በማንነት አለመግባባት ስም ቢቀርብለት ሌሎች ታሪካዊ የአሰፋፈር ዳራዎችን በማካተት አሰፋፈርንና ፍላጎትን መሰረት አድርጎ በራሱ ጊዜ ዉሳኔ እንደሚሰጥበት ከወዲሁ መገመት አያዳግትም። የሚያደናግር አሰፋፈር፣የህዝብ ፍላጎት እና የቅርብም ሆነ የሩቅ ተጨማሪ ዲሞግራፊያ መረጃዎች በሌለበት ሁኔታ ህዝበ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ሊደርግ አይችልም።

# 5. ጥያቄዉ የማን ሆነ?

በተጠቀሱት አካባቢዎች ያለዉ ጥያቄ ላለፉት 25 ዓመታት የነበረ ስለመሆኑ እየተነገረንም እስከአሁን ባገኘነዉ መረጃ መሰረት ለሰዉ ልጆች ህልፈት የዳረገዉ ጉዳይ በህጋዊ መንገድ አልቀረበም። በተለይ የነዉጥ ሀይሎች የራስን እድል በራስ የመወሰን ሉኣላዊ ስልጣን ያላቸዉ ብዙሃኖች ጥያቄ ስለመሆኑ ማረጋገጫ የላቸዉም። በትግራይ ክልል የሚኖረዉ የወልቃይትም ሆነ የፀገዴ አካባቢ

ህዝብ ጥያቂዉን ህግና ስርአት በሚፈቅደዉ መሰረት ለአካባቢዉ መስተዳድር እና ለክልሉ መንግስት እስካላቀረበ ድረስ የሉኣላዊ ስልጣን ባለቤት የሆነዉ ህዝብ ጥያቄ ነዉ ማለት አይቻልም። በትግራይ ክልል ያለዉን ህዝብ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ጉዳይ ኢ-ህገመንግስታዊ በሆነ መንገድ ከክልሉ ዉጭ በሆኑ አካላት የሚቀርብ የማንነት ጥያቄ ከአምባገነንነት ያለፈ ተግባር አይሆንም። በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት አስተዳደር ስር ያለ ህዝብ የማንነትም ሆነ የድንበር ጥያቄ ካለዉ ለራሱ ክልል በህጋዊ መንገድ ማቅረብ ይችላል። ቢሆንም ግን በትግራይ ክልል ስለሚገኝ ህዝብ የማንነት ጉዳይ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት መፍትሄ እንዲሰጥበት የማቅረብ መብት በህገመንግስት አልተደነገገም ሊደነገግም አይችልም። የነዉጥ ተልእኮዎችን ስናጤናቸዉ ግን የአንድን ሉኣላዊ የአስተዳደር ክልል ስልጣንና በዉስጡ የሚኖርን ህዝብ ህገመንግስታዊ መብት በማይመለከተዉ ክልልና ህዝብ እንዲፈታ ከመፈለግ የመነጬ አንባገነናዊ ፍላጎቶች አሏቸዉ። ስለሆነም እስከአሁን የታየዉ ክስተት ምንጭና ፍላጎት በእርግጥም የማይመለከተዉ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ህገመንግስታዊ ስርአታችንን በሀይል ለማፍረስ ያቀጣጠሉት የጥፋት ተልእኮ ነዉ። ይህንን በእንጭጩ ለመቅጨት የሚያስችሉ እርምጃዎች አልተወሰዱም። ህዝቡን የሚያስገነዝቡ መግለጫዎች በወቅቱ አልተሰጡም። ከህዝቡ ጋር በወቅቱ መወያየት አለመቻል ወይም ችግሩ ስርአት ባለዉ መንገድ እንዲቀርብ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ተነሳሽነት አለመዉሰድ ደግሞ የሚመለከታቸዉ የአመራር አካላት ድክመትና ድርሻ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ግን እስከአሁን በነበረዉ ሁኔታ ጥያቄዉ የሚመለከተዉ ህዝብ አልነበረም ብቻ ሳይሆን የተፈፀሙት ክስተቶች ላለፉት 25 ዓመታት ተከባብረዉና ተደጋግፈዉ በኖሩት በትግራይ እና በአማራ ህዝቦች ላይ ጥቁር ነጥብ ጥሎ ያለፈ የሰዉ በላዎችና ወንጀለኞች ተግባር ነዉ።

*ሲጠቃለል የጥያቄዉና የብጥብጡ ምንጭ እነ ፕሮፌሰር ጌታቸዉ እና ተከታዮቻቸዉ ናቸዉ። በትግራይ ህዝብም ሆነ በሌሎች ብሄረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ተፃራሪ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ለዓመታት የቆየ የተዳፈነ እሳት ነዉ። እነዚህ የብሄረሰቦች ጠላቶች ከትላንት እስከዛሬ ከሚያቀነቅኑት ዉስጥ አንድ ሀሳብ ጨልፈን እንመልከት።*

*"... የአንድ አገር ዜጎች ነን በሚል ፈሊጥ ብቻ ቱርኮች በኩርዶች፣እስራኤላዊያን በአረቦች፣ እንግሊዞችም እንደዚሁ በአይሪሾች ለመገዛት ፈቃደኞች ሊሆኑ ይችላሉን? አይችሉም። ፈቃደኞች ሊሆኑ አይችሉም።....."( መምህር ገብረኪዳን ደስታ የፕሮፌሰር ጌታቸዉ ሀይሌን ሀሳብ እንደጠቀሱት። ገፅ 253፣ ፓራግራፍ 1፣"የትግራይ ህዝብና የትምክህተኞች ሴራ ከትናንት እስከዛሬ")። ፕረፌሰር ጌታቸዉ ይህን የተናገሩት 60 ሺህ ያህል ለመስዋእትነት እና 100ሺ ያህል ለጉዳት ከዳረገ በኋላ እንደሌሎቹ ብሄር ብሄረሰቦች እራሱን በራሱ ከማስተዳደር ያለፈ የተለየ ጥቅም ያላገኘዉን የትግራይን ህዝብን ነዉ። ይህ ህዝብ በቀድሞዎቹ ስርአቶች ያለአግባብ ወደትግራይ ተካለዉ የነበሩ በተፈጥሮ ሀብት የበለፀጉና ለም መሬቶች ወደአፋር እና አማራ ክልሎች እንዲተላለፉ ሲደረግ የታገለለት ዓላማ በመሆኑ በፀጋ ከመቀበል በስተቀር እንደትምክህተኞች አልተንጫጫም። እነፕሮፌሰር ጌታቸዉ ሀይሌ ግን በትግራይ ህዝብ ላይ የያዙት ስር የሰደደ ጥላቻ በመሰረቱ ሲመዘን በሌሎች ብሄር ብሄረሰቦችም ላይ ያነጣጠረ ነዉ። ይህን የሞተ አስተሳሰብና ጭፍን ጥላቻ በአንድ በኩል የራስን እድል*

*በራስ በመወሰን ህገምንግስታዊ መርህ በሌላ በኩል ደግሞ ለአገራችን ከማይመጥነዉ ዉራጅ ከሆነዉ የሊብራል ዲሞክራሲ አስተሳሰብ አንፃር መገምገም ተገቢ ይሆናል።*

*የራስን ኢድል በራስ የመወሰን መርህ በመሰረቱ በአሰፋፈር፤በቋንቋና በብሄራዊ መሰረት ተመሳሳይ የሆነ ህዝብ እራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር፤በማንነቱ፣በቋንቋዉ፣በባህሉ፣በታሪኩ እንዲወስን፣እንዲጠቀም እና እንዲያሳድግ የተሟላ መብት ያስከብራል። ከዚህ አኳያ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ የትግራይም ሆነ የሶማሌ ህዝብ እራሱን በራሱ እንጂ ሌሎችን "አልገዛም"(በእነ ፕሮፌሰር ጌታቸዉ ቋንቋ)።የቤኒሻንጉልም ሆነ የጋምቤላ፤ የኦሮሞም ሆነ የሀረሪ፣ የወላይታም ሆነ የስልጢ፣የአማራም ሆነ የከንባታ፤የአፋርም ሆነ የሲዳማ ብሄር ብሄረሰብ "እየተገዛ" ያለዉ ከአብራኩ በወጡ ልጆች እና በራሱ ምርጫ ብቻ ነዉ። የአካባቢዉ የጥንት መሰረት እነርሱዉ በመሆናቸዉ የአስተዳደርም ሆነ የፖለቲካ ሉአላዊ ስልጣን የእንርሱዉ ነዉ።በአካባቢዉም ሆነ በክልሉ ጉዳይ ላይ ፈላጭ ቆራጭ እንዲሆን የተላከበት ብሄርም ሆነ ብሄረሰብ የለም። በአሁኑ ጊዜ የብዙሃንን እና ንኡሳንን ቁጥር እየጠቀስን እገሌ ብሄር በማይመለከተዉ አካባቢ የመግዛትና የማስተዳደር ስልጣን ሊሰጠዉ ይገባል ወይም አይገባም የሚል ክርክር እንድናነሳ የሚጋብዘን አስተዳደራዊ፣ፖለቲካዊም ሆነ ህግመንግስታዊ ስርአት የለንም። በተግባርም አልታየም።የትግራይ ህዝብ "እየገዛ" ያለዉ እራሱን በራሱ እንጂ የአማራን ወይም ሌላዉን ብሄር እና ብሄረሰብ አይደለም።ሌላዉም እንደዚያዉ። ስለሆነም እገሌ ብሄር ሊገዛን አይገባም የሚለዉ በብሄሮችና ብሄረሰቦች ጥላቻ ላይ የተመሰረተዉ ቅስቀሳ እና አንዱን ብሄር በሌላዉ ላይ የማነሳሳት ዛር በሰላምና በመከባበር እንዳንኖር የሚረጬት መርዝ ከመሆን ያለፈ እዉነታ የለዉም።*

*የአስተሳሰብ ችግርነቱ በዚህ አያበቃም። አስተሳሰባቸዉ በጣም ጠባብና ትምክህት የወለደዉ ነዉ። ሌላዉ ቢቀር እናራምደዋለን የሚሉትን የሊብራል ዲሞክራሲ ርእዮተዓለም እና የአከላለል ስርአት የሚፃረር ነዉ። ከርእዮተዓለማቸዉ ጋር የተጣላ አስተሳሰብ ነዉ። እንደተገለፀዉ የብሄር ብሄረሰቦች ሉአላዊ ስልጣን ዋነኛ መገለጫ የክልላዊ አስተዳደሮች ህልዉና መጠናከር ነዉ። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከስልጣናቸዉ ቆርሰዉ ባዋቀሩት ፌዴራላዊ መንግስት ዉስጥ የጋራ ሚና እና ድርሻ ይኖራቸል። በዚህ የጋራ ሚና ስልጣን እንዲይዝ ህዝባዊ ይሁንታ የተሰጠዉ የፖለቲካ ድርጅት በዉስጣዊ ድርጅቱ በሚያደርገዉ ምክክርና መግባባት የስልጣን ክፍፍል ስርአቱን ይመራል ያስተዳድራል። በዚህ አግባብ ለምሳሌ የድርጅቱ ሊቀመንበር እና የሀገሪቷ ጠቅላይ ሚኒስትር በቁጥር ንፅፅር ሳይሆን በብቃት ላይ ተመስርቶ ብዙ ወይንም ትንሽ ቁጥር ካለዉ ብሄረሰብ የመጣ ሊሆን ይችላል። እዚህ ላይ ልብ ማለት የሚኖርብን ይህ ግለሰብ የሚወክለዉም በበላይነት የሚያስተዳድረዉም የፖለቲካ ድርጅቱን የመሰረቱትን ኦህዴድን፣ህወሓትን፣ብኣዴንን እና ደኢህዴንን፤ ሌሎችን ክልሎች ለማስተዳደር የተመረጡትን አጋር የፖለቲካ ድርጅቶችን እንደዚሁም በየክልሉ ያሉ ብሄር ብሄረሰቦችን እንጂ የመጣበትን ብሄረሰብ ብቻ አይደለም። ብሄራዊ ማንነቱ ብዙ ወይንም ትንሽ ቁጥር ካለዉ ብሄረሰብ የመሆኑ*

*ጉዳይ የአንድን ብሄረሰብ የበላይነት አያንፀባርቅም። ቢፈልግም እንኳ ህገምንግስታዊ፣ድርጅታዊና ፌዴራላዊ የአስተዳደር ስርአታችን አይፈቅድለትም። እንደዚያ ቢሆን ኖሮ በዚህች አገር የሚመረጥ ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ፕሬዚደንት ባልኖረ ነበር። እነ ፕሮፌሰር እገሌ ግን በአንድ በኩል የብሄር ብሄረሰቦችን የራስን እድል በራስ የማስተዳደር ስልጣንን የሚያጎናፅፈዉን ሳይሆን የግለሰቦችን መብት ብቻ የሚያረጋግጠዉን አሃዳዊ የህገመንግስት ስርአት ያራምዳሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ይህንኑ ዉራጅ አስተሳሰብ በመቃወም በፌዴራል ደረጃ የሚሾምን አንድ ወይም ሁለት ሰዉ በመቁጠር ከአናሳ ነዉ ወይንም ከብዙ ነዉ፤ ይህኛዉ መግዛት አለበት ያኛዉ መግዛት የለበትም እያሉ ያዉኩናል። እርስበርስ እንድንባላ ነዉጥ ያስነሱብናል። ከእንግዲህ በዚህች አገር ተቀባይነት ሊኖረዉ የማይችለዉን አሃዳዊ የአስተዳደር ስርአት የሚያራምድ ግለሰብ፣ቡድንም ሆነ የፖለቲካ ድርጅት በግልባጩ ከጥቂቶች ወይም ከብዙዎች የመጣ እያለ ከራሱ ጋር መጣላት ባልተገባዉ ነበር። ዳሩ ግን ከራስ አስተሳሰብ ጋር የመጣላቱ መሰረታዊ ምክንያት የእዉቀት ማነስ አይደለም። መሰረታዊዉ ምክንያት በብሄር ብሄረሰቦች ላይ ያለ የገነነ ንቀት እና ጥላቻ ነዉ። መሰረታዊዉ ችግር በዚህች አገር የብሄረሰቦችን ህልዉና ላለማየት ካለ ፍላጎት የሚመነጭ ነዉ። በመሆኑም ለጎንደርና ለአካባቢዉ በአጠቃላይ ደግሞ ለአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሀብትና ንብረት እንደዚሁም ለንፁሃን ህይወት መጥፋት ጭምር እንደተዳፈነ እሳት ሆኖ ያገለገለዉ ይህ በጥላቻ ላይ የተመሰረተዉ አስተሳሰብ እስካልጠፋ ድረስ ብሄር ብሄረሰቦች ትግላችንን አናቋርጥም። የቸገረን ጉዳይ ግን በአመክንዮ ታግሎ ማሸነፍ አለመቻል አይደለም። ከዚህ ይልቅ ችግር የሆነብን ለህዝባችን እጥፍ ድርብ አገልግሎት ልንሰጥ የሚገባንን ጊዜ ከእነርሱ ጋር ለመነታረክ ሲባል ማባከናችን ነዉ። ችግራችን በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት የሌለዉ አስተሳሰብ የማቅረባቸዉ ጉዳይ ሳይሆን ለአሁኑም ሆነ ለመጪዉ ትዉልድ እድገትና ብልፅግና የምንተጋበትን ጊዜ በእነርሱ ምክንያት ማባከናችን ነዉ። ችግራችን አንዱን ወይንም ሌላዉን ብሄር ከፍና ዝቅ የማድረግ ተግባራቸዉ እና የግጭት ተልእኮአቸዉ ተቀባይነት አግኝቶ ፍሬ ያፈራላቸዋል የሚል ፍርሃት ሳይሆን በየጊዜዉ የሚለኩሱትን እሳት በማጥፋት የልማት ጊዜአችንን እያባከኑብን ስለሆነ ነዉ። ችግራችን በእነዚህ የህዝብ ጠላቶች ምክንያት በልማት ዉጤቶቻችን እና በህዝባችን ህይወት ላይ እየደረሰ ያለዉን ዉድመት ለመታደግና መልሶ ለማልማት የምናጠፋዉን ጊዜ እያባባሱብን በመሆኑ ነዉ። ችግራችን የእነዚህ እሳት አቀጣጣዮች “የእሳት አደጋ መከላከያ ኤጀንሲ” ሆነን እንድናገለግል እያስገደዱን ስለሆነ ነዉ። የቸገረን ይህ እንጂ ከእንግዲህ በዚህች አገር ዉስጥ እነዚህ አስተሳሰቦች ስልጣን ለማግኘት የህዝብ ተቀባይነት ያገኛሉ የሚል ፍርሃት ስላለብን አይደለም። በመሆኑም በትግራይ እና በአማራ ህዝብ መካከል ግጭት በመፍጠር ከትርምስ ለማትረፍ የሞከሩ ቢሆኑም አልተሳካላቸዉም። ለወደፊቱም አይሳካላቸዉም። ህዝቡና የሁለቱም ክልሎች መስተዳድሮች በቅድሚያ የዉስጥ ችግሮቻቸዉን በማጥራት አሉ የሚባሉ የህዝብ ጥያቄዎችን በህግና በህግ ብቻ መፍትሄ እንዲያገኙ አፋጣኝ እርምጃ እንደሚወስዱም አንጠራጠርም።*

## 6. ህዝብህ በሌሎች አካባቢዎች ተከብሮና መብቱ ተጠብቆ እንዲኖር ከፈለግህ ካንተ ጋር የሚኖሩትን ሌሎች ህዝቦች እንደራስህ አድርገህ ጠብቃቸዉ።

የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስትም ይሁን ሌሎች ክልሎች በዉስጣቸዉ ያሉ ሌሎች ብሄር ብሄረሰቦችን የመጠበቅና የመንከባከብ መንግስታዊ ሀላፊነት አለባቸዉ። የዓለምአቀፍ ሰብአዊ መብት ህግጋት ሰብአዊ መብትን በተመለከተ በመንግስታት ላይ ሶስት መሰረታዊ ግዴታዎችን ይጥላሉ። ወደዝርዝሩ ሳንገባ የማክበር፣የማስከበር እና የመከላከል ግዴታዎች ናቸዉ። መከላከል ሲባል ማንኛዉም የሰዉ ልጅ በሶስተኛ ወገን ጥቃት እንዳይደርስበት ለመታደግ የሚያስችሉ ቅድመሁኔታዎችን ከማሟላት አልፈዉ ጥቃት ሲደርስባቸዉም እንደራሳቸዉ ዜጎች ወይም ነዋሪዎች አፋጣኝ እርምጃዎችንና መፍትሄዎችን መስጠት ይጠበቅባቸዋል። ስለሆነም በአንድ ክልል መጠነ ሰፊ የሆነ የሰብአዊ መብት ጥሰት ከተፈፀመ አንድም  በራሱ አቅም መከላከል ይኖርበታል አለያም ከአቅሙ በላይ ከሆነ የፌዴራል መንግስቱ ድጋፍ እንዲያደርግለት በአፋጣኝ መጠየቅ ይጠበቅበታል። ይህን ባለማድረጉ ምክንያት ከሌላ አካባቢ ፈልሶ በሚኖረዉ ህዝብም ሆነ በክልሉ ነዋሪ ላይ ቅጥ ያጣ ጉዳት ከደረሰ በቀጥታም  ባይሆን በተዘዋዋሪ የክልሉን መንግስት ድክመት ያሳያል። የትኛዉም የህብረተሰብ ክፍል በስጋት ዉስጥ መኖር የለበትም። በተረጋጋ ስንልቦና ወጥቶ መግባት አለበት። ከኤርትራ እና ከሶማሊያ ተሰደዱ ወገኖቻችንን ደግፎና ተንከባክቦ የያዘ ህዝብና አገር በዜግነትና በነዋሪነት ቋሚ ተሰላፊ በሆኑ ወገኖቹ ላይ የሶስተኛ ወገኖች ተጠቂ እንዳይሆኑ መከላከል ግዴታዉ ነዉ። የፌዴራልም ሆነ የክልል ህገመንግስቶቻችን የዜጎችን ከቦታ ወደቦታ ተንቀሳቅሶ የመስራት እና ሀብት የማፍራት መብት አረጋግጠዋል። የዉጭ አገር ኢንቨስተሮችን ለመሳብ አበሳችንን በምናይበት አገር ዉስጥ ከአንድ ክልል ወደሌላ ክልል ተጉዞ ሀብትና ንብረት ያፈራ ወገናችንን ጥበቃ የማናደርግለት ከሆነ ሁሉም ነገራችን የዉሸት ነዉ። ዜጎች የክልሎችን አስተዳደራዊና ህግመንግስታዊ ግዴታዎች እስካሟሉ ድረስ እኩልነታቸዉ ሊከበር ይገባል። ሁሉም ክልልሎች ወደሌሎች ክልሎች የተሰማሩ ወገኖች አሏቸዉ። የአንደኛዉ ብሄር ጉዳት ለሌሎቹ ብሄሮች ህመም መፍጠር መቻል አለበት። በዚህ አስተሳሰብ መጓዝና ማስተዳደር ካልቻልን ተከባብሮ ስለመኖር እና ስለኢትዮጵያ አንድነት መጠናከር፤ስለአንድ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መፍጠር የፃፍናቸዉም ሆኑ በየመድረኩ የምንደሰኩራቸዉ ከማሰልቸት ያለፈ ትርጉም አይኖራቸዉም። ሆኖም ግን በዚህ ጉዳይ ላይ የአንበሳዉን ድርሻ የሚስደዉ ስለመብትና ዲሞክራሲያዊ ስርአት እየዘመረ የብሄረሰቦችን ህልዉና ለማጥፋት የተሰለፈዉ የነዉጥ ሀይል ነዉ። የፈለጉትን አይነት ጥያቄ በህጋዊ መንገድ አቅርቦ መልስ ማግኘት የሚቻልበት አገር ዉስጥ ነን። በአምባገነናዊ መንገድ የሰዉ ልጆችን፣ የክልሉ ህዝብና መንግስት አንጀታቸዉን አስረዉ ያፈሩትን ሀብትና የልማት ተቋማት ማዉደም በርግጥም የመብት ጥያቄ አለኝ ከሚሉ ቡድኖች አይጠበቅም። መብት እንዳለን ሁሉ ግዴታም ተጥሎብናል። ዳሩ ግን ከላይ እንደጠቀስነዉ እነዚህ የነዉጥ ሀይሎች በዉሃ ላይ እንደሚኖር ድንጋይ የማይገባቸዉ ወይም ደግሞ ለእነርሱ ሲሆን የግዴታ እና የዲሞክራሲያዊ ስርአት ጉዳይ እንዲገባቸዉ  የማይፈልጉ ደደቦች ስለሆኑ የየክልሉ መንግስታትም ሆኑ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ከእነርሱ ብዙም አይጠብቁም። ለማንኛዉም የሰዉ ልጆችን እና እንደሰዉ ልጅ ብዙ ተቸግረን ያሳደግናቸዉን/የፈራናቸዉን/ የልማት ዉጤቶቻችንን  ከትዉልድ ወደትዉልድ እንዲተላለፉ የመጠበቅ ግዴታ የሁሉም አካላት ድርሻ ነዉ። በተለይ ደግሞ መንግስታትም ሆኑ ክልሎች በዉስጣቸዉ የሚኖሩ ህዝቦችን ህልዉና በእኩል አይን ተመልክተዉ የመጠበቅ ግዴታ ተጥሎባቸዋል። ይህን ካላደረጉ በሌሎች አካባቢዎች በሚኖሩ ወገኖቻቸዉ ላይ ተመሳሳይ ህገወጥ ተግባር እንዲፈፀም ያበረታቱ ያህል ይቆጠራል።

*በስርአትና በህጋዊ አኳኋን ከተነጋገርን የማይፈታ ችግርም ሆነ የማይመለስ ጥያቄ አይኖርም!!!*

*ሰላም ለሁላችን!*